# ግጭት እና ኮቪድ-19 በኢትዮጵያ የሴቶች ፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ያሳደሩት ተፅዕኖ

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር

ታህሳስ : 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ : ኢትዮጵያ

NATIONAL DEMOCRATIC INSTITUTE

USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE

Ethiopian Women Lawyers' Association

# ማሳሰቢያ

ይህ ጥናት እንዲካሄድ ያደረገዉ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ሲሆን በጥናት ዉጤቱ ሪፖርት ላይ የተገለጹት ግኝቶች ፣ ትርጓሜዎች እና ማጠቃለያዎች የጥናት አድራጊ ቡድኑ ኃላፊነት እንጂ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር አስተዳደር ፣ የቦርድ አባላት እንዲሁም የባለድርሻ አካላት ሃላፊነት ሊሆን አይችልም፡፡

በዚህ ጥናት ዙሪያ ላለዎት ማንኛውም ጥያቄዎች እባክዎን በሚከተሉት አድራሻዎች ያነጋግሩን።


**የቢሮ አድራሻችን፡-** አዲስ አበባ ፡ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ፡ ሜክሲኮ/ ቡልጋሪያ አካባቢ ከሚገኘዉ ሚካኤል ቤተክርስቲያን አጠገብ

**ስ.ቁ፡-** +251-11-508783

**ኢሜል፡-** info@ewla-et.org

**ፖ.ሳ.ቁ፡-** 13760

# ምስጋና

ይህ ጥናት የተካሄደው በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ሲሆን ሪፖርቱ በርካታ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል። ስለሆነም በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ በጥናት ሂደቱ የተሳተፉ እና የተሻለ ጥራት ያለው ውጤት እንድናገኝ የረዱንን ሁሉ አካላት እናመሰግናለን። ከሁሉ አስቀድሞ ግን በውይይቱ ላይ በነፃነት በመሳተፍ አስተዋፅዖ ላደረጉ እና በርዕሰ-ጉዳዩ ላይ ሃሳባቸውን ላቀረቡ ምላሽ ሰጪዎች ከልብ የመነጨ ምስጋናችንን እናቀርባለን። ያለነሱ ጥልቅ ተሳትፎ እና ግብአት ጥናቱ በተሳካ ሁኔታ ሊካሄድ አይችልምና። በጥናት ሂደቱ ወቅት ታላቅ አስተዋፅዖ ላበረከቱ የፖለቲካ ባለሙያዎች እና የስራ ኃላፊዎች ላደረጉልን ቀና ትብብር ልባዊ ምስጋና እና አድናቆታችንን እንገልፃለን።

# መቅድም

ግጭት እና ኮቪድ-19 በጾታ እኩልነት ላይ ተጽእኖ ያስከተሉ አስደንጋጭ ክስተቶች ናቸው። ምንም እንኳን ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ተፅዕኖዎቹን ማስወገድ ባይችሉም የጉዳቱ ክብደት ግን በጾታ ላይ ተመስርቶ ይለያያል። በዓለም ላይ እየታዩ ያሉ ለውጦች እንደሚያሳዩት ግጭት እና ኮቪድ-19 ሴቶችን በተለየ መልኩ ጎድተዋል። ጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች እና ሰብአዊ ቀውሶች ብቻ ሳይሆን በፖለቲካ ተሳትፎ ረገድም  የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ በይበልጥ የሚጎዱ ሆኖ ተገኝቷል። እነዚህ ስጋቶች ከወንዶች ይልቅ በሴቶች ላይ ይከብዳሉ። ስለዚህ ሶስት በግጭቶች የተጎዱ ክልሎች ማለትም አማራ ፣ አፋር እና ኦሮሚያን እንደ ጥናት አካባቢ አድርጎ በመጠቀም የጥናቱ ዋና አላማ ግጭቶች እና ኮቪድ-19 በኢትዮጵያ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ያላቸውን ተፅእኖ መገምገም ነበር። ለጥናቱ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን ጥራትን መሰረት ያደረገ የአቀራረብ ዘዴ ላይ የተመሰረተ ጥናት ተካሂዷል። ቁልፍ መረጃ ሰጭ ቃለ መጠይቆች እና የቡድን ውይይቶችን በመጠቀም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ፣ ከሴቶች ፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ፣ ከተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተዉጣጡ ሴት ፖለቲከኞች እንዲሁም በዞንና በወረዳ ደረጃ ካሉ ሴት አመራሮች የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን መሰብሰብ ተችሏል። እነዚህም በሶስቱ ብሄራዊ ክልሎች ውስጥ የተካሄዱ ናቸው። በዚህም መሰረት በኮቪድ-19 ሳቢያ በተደነገጉ የእንቅስቃሴ ገደቦች እና በተከታታይ እየታዩ ያሉ ግጭቶች በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ያሳደሩት ተጽዕኖ የደህንነት ስጋት ፣ የባህላዊ ሚናዎች መነቃቃት ፣ የወንዶች የውሳኔ አሰጣጥ የበላይነት ፣ የደህንነት እጦት መጨመር እና የእንቅስቃሴ ገደቦች መበራከት ፣ የደህንነት ጥበቃዎች አድሏዊነት ፣ የወንዶች መደበኛ ያልሆኑ የግንኙነት መረቦች ሁኔታ እየጨመረ የሴቶችን ሚና ዝቅ አድርጎ መመልከት እና የአስቸኳይ/አጣዳፊ ሁኔታዎች ተለዋዋጭነት መጨመር ናቸው።

በመጨረሻም እንደ ምክረ ሃሳብ የተጠቆሙት ከስጋት ጋር በተያያዘ የሴቶችን አቅም ማጎልበት ተነሳሽነት ማጠናከር ፣ ስጋት/ቀውስ ተኮር የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ስትራቴጂን ማዘጋጀት እና በመጨረሻም ሴቶችን መሰረት ያደረጉ የግንኙነት መረቦችንና አደረጃጀቶችን ማጠናከር ቀውስ በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያስከትላቸውን ተፅእኖዎች ለመቀነስ መሰረት ናቸው።

# ምህፃረ-ቃላት እና አጭር መግለጫዎች

**EWLA፡** የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር
**FGDs፡** የትኩረት ቡድን ውይይቶች
**GoE ፡** የኢትዮጵያ መንግሥት
**KIIs፡** ቁልፍ መረጃ ሰጭ ቃለ-መጠይቆች
**NDI፡** ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ተቋም
**ህወሓት፡** ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ
**ኦነግ** - የኦሮሞ ነፃነት ግንባር
**VAW፡** በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት

# ማውጫ


የጥናቱ ዳራ........................................................................................ 1
የጥናቱ መነሻ ...................................................................................... 3
የጥናቱ ዓላማዎች................................................................................. 5
የጥናቱ ዘዴ......................................................................................... 5
የጥናቱ አስፈላጊነት................................................................................. 6
የጥናቱ ወሰን....................................................................................... 7

**ምዕራፍ ሁለት**

**ግጭት ፣ ኮቪድ-19 እና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ በኢትዮጵያ**.................. 9
ቀውስ ፣ ስርዓተ ጾታ እና ዲሞክራሲ........................................................... 9
ቀውስ እና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ መቀነስ...........................................10
ኮቪድ-19 ፣ ግጭት እና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ በኢትዮጵያ................................ 11
ግጭት እና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ.............................................................13
ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ እና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ..........................................14
ግጭት እና ኮቪድ-19 በኢትዮጵያ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ያሳደሩት ተጽዕኖ - ከአፋር ፣ ኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ኬዞችን በመውሰድ የተደረገ ጥናት.................................................................. 17
በኢትዮጵያ በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ሂደቶች የሴቶች ተሳትፎ................ 29
የንፅፅር ግምገማ በክልል ከተሞች..........................................................30

**ምዕራፍ ሶስት**

ማጠቃለያ እና ምክረ ሃሳቦች...................................................... 32
ማጠቃለያ.......................................................................................32
ምክረ ሃሳቦች.................................................................................... 36

# 1.የጥናቱ ዳራ

የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ዲሞክራሲን እና ዘላቂ ልማትን ለማስፈን ለማንኛውም ዓለም አቀፍ ዓላማዎች ቅድመ ሁኔታ ነው። እንደ የምርጫ ክልል አባላት ፣ ተወዳዳሪዎች ፣ የተሾሙ ኃላፊዎች ወይም የምርጫ አስተዳዳሪዎች ያሉ የተለያዩ ቅጾችን ሊይዝ ይችላል። ነገር ግን የሴቶች ሙሉ እና ውጤታማ የፖለቲካ ተሳትፎ በሌለበት ዴሞክራሲ ሊሳካ አይችልም። በተመሳሳይ መልኩ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊወክሏቸው ያሰቧቸውን ማህበረሰቦች በተለይም ሴቶቹን በበቂ ሁኔታ ማበረታታት ካልቻሉ ህልውናቸውን ችግር ውስጥ መጣላቸው የማይካድ ነው (አሽልድ ፣ 2010፡ ታጃሊ ፣ 2013 እና ውባንተ ፣ 2021)። ሁሉን አቀፍ እና ዘላቂ ልማትን እንዲሁም ሰብአዊ መብቶችን ማስጠበቅ በፖለቲካ ተሳትፎ መሻሻልና የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን በማረጋገጥ ስኬታማ ሊሆን ይችላል (ኮሬጅ ኤንደ ፎርጌት ፣ 2019)። ከዚህ እውነታ የተነሣ በፖለቲካ ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን የማስጠበቅ የፓራዳይም ለውጥ አስፈላጊነት በተለያዩ ተዋናዮች አጀንዳዎች ላይ የበላይ ሆኖ ቆይቷል። በመሆኑም ባለድርሻ አካላት የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ አስፈላጊነት በሀገር ውስጥ እና በአለም አቀፍ መድረክ በቅንነት ሲያቀርቡ ቆይተዋል (ሲንድሁጃ ፣ ኤነድ ሙሩጋን፣ 2017)።

ለምሳሌ፡- በ1995 በቤጂንግ የተካሄደው አራተኛው ዓለም አቀፍ የሴቶች ኮንፈረንስ በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ረገድ የሥርዓት ለውጥን ፍለጋ መሠረት ያደረገ ነበር። ኮንፈረንስ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ቀጣይነት ያለው የሥርዓተ-ፆታ ልዩነት ትኩረት ሰጥቷል ፤ ሴቶች በመደበኛ ፖለቲካ አለመቀጠላቸው በዲሞክራሲ እና በጾታ እኩልነት ላይ ያለውን ተጽእኖ አስምሮበታል (UNDAW ፣ 2005)። እንደ ቀጣይ ሂደት የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት በሴቶች ሰላም እና ፀጥታ ላይ ውሳኔ 1325 በማፅደቅ-ይህም በግጭት አፈታት እና ሰላም ግንባታ ላይ የሴቶች ተሳትፎ እያደገ መምጣቱን የሚያሳይ ነው። ቢሆንም እንደ ፖለቲካዊ ባህል (የወንድ የበላይነት) ፣ የፋይናንስ አቅም ማጣት ፣ ማህበራዊ-ባህላዊ ሁኔታዎች ፣ ሁከት ፣ ቅንነት የጎደለው እና ሴቶችን ከፖለቲካ

ፍላጎት ማግለል/ጭቆና፣ በሴቶች የሰላም ድርድር ላይ የሚሳተፉትን ፕሮቶኮሎች ተግባራዊ ለማድረግ አሁንም ውስን ነው። በመሆኑም ሴቶች በሁሉም የውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎች ዝቅተኛ ውክልና አላቸው (ዲላንዞ ፣ 2019: ፋልች ፣ 2010 ፤ ኦጉአዲማ ኤት አል 2021)።

በአህጉር ደረጃ የአፍሪካ አጀንዳ እ.ኤ.አ 2063 የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሻሻል የጾታ እኩልነት ባህልን እና መልካም አስተዳደርን በማጎልበት ቁርጠኝነትን በማፅደቅ የሥርዓተ-ፆታ ክፍተቶች ላይ ትኩረት ለመሳብ ፣ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሻሻል እንዲሁም የሚታይ እድገት ለማምጣት ተጨባጭ ማስረጃዎች አስፈላጊ መሆናቸውን አምኗል። በተጨማሪም የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚመለከቱ እርምጃዎችን ያካተተው የማፑቶ ፕሮቶኮል አህጉሪቱ በፖለቲካ ውሳኔ አሰጣጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማሳደግ ያላትን የረዥም ጊዜ ቁርጠኝነት አሳይቷል (IDEA, 2021) ፤ ምንም እንኳን የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም ሴቶች ከአፍሪካ የፖለቲካ መድረክ ውጭ እንዲሆኑ ተገድደዋል። የፖለቲካ ምህዳሩ እና ሁኔታዎች በፖለቲካ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ በተደጋጋሚ የሚቃረኑ እንደመሆናቸው በአፍሪካ ያሉ ሴቶች የአገራቸውን አቅጣጫ በመቅረጽ ድምጻቸውን ለመግለጽ ቢሞክሩም ብዙ መሰናክሎች ስላጋጠሟቸው በአብዛኛው አልተሳካላቸውም (ኮውሬጅ እና ፎርጌት : 2019)። በተለይም በተፈጥሮም ሆነ በሰዉ ሰራሽ አደጋዎች ወቅት ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ለአሉታዊ ተጽእኖዎች ተጋላጭ ናቸው። ለምሳሌ:- SIDA (2015) እና ጆርጅ (2021)፣ የግጭት እና የድህረ-ግጭት ሁኔታዎች እንዲሁም የአለም አቀፍ ወረርሽኞች ሴቶችን ለፆታ ተኮር ጥቃት፣ ለኑሮ ውድነት መጋለጣቸውንና ከውሳኔ ሰጪነት መገለላቸውን አረጋግጠዋል። በተጨማሪም ግጭቶች እና ዓለም አቀፍ ወረርሽኞች በሴቶች ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጉዳዮች ላይ ከሚያደርሱት ልማዳዊ ተፅእኖ ባሻገር በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያሳድሩት የተጽዕኖ አዝማሚያዎች እየታዩ ነው። እንደ ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት (2020) በወረርሽኙ ግጭቶች የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ያሉ ቀውሶች ይከሰታሉ።

ለሁሉም ባለድርሻ አካላት የፖለቲካ ምህዳሩ እየጠበበ እና አጠቃላይ የፖለቲካ ስርዓቱ ከበለጠ የምክክር አሰራር ወደ "ትእዛዝ እና ቁጥጥር ስርአት ይሸጋገራል" ፤ ለሴቶች ይህ አሰራር በተለይ በፖለቲካ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ድምፃቸውን እና ውክልናቸውን ከማጣት አንፃር ብቻ ሳይሆን የአካል ክልከላዎች እና የመረጃ ክፍተቶች (NDI : 2020) ችግርም አለበት።ስለሆነም ወረርሽኙን ፣ ግጭቶችን እና የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮችን በሴቶች ማህበራዊ ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ለመለካት ከባህላዊ እይታ በተጨማሪ ግጭቶች እና ወረርሽኞች የሴቶችን እኩል እና ትርጉም ያለው የፖለቲካ ተሳትፎ እንዴት እንደሚያደናቅፉ መመርመር በጣም አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ጥናቱ ኮቪድ-19 እና ግጭቶች በኢትዮጵያ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያደርሱትን ተፅእኖ ለመገምገም የተካሄደ ሲሆን የአማራ ፣ ኦሮሚያ እና አፋር ክልሎችን እንደ ጥናት አከባቢ አድርጎ ወስዷል።

## 2. የጥናቱ መነሻ

በማደግ ላይ ባሉም ሆነ በበለጸጉ አገራት ሴቶች በአደጋዎች ወቅት በእጅጉ ይጎዳሉ። በተለይ በአደጋ ጊዜ እራሳቸውን ለመከላከል እና በማህበራዊ ኢ-ፍትሃዊነት እና በፆታ ልዩነት ሳቢያ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጥፋት ለመቀነስ የተጋለጡ እና አቅም የሌላቸው ናቸው (SIDA ፣ 2009)። ለምሳሌ የትጥቅ ግጭት ፆታን አይመርጥም (ገለልተኛ አይደለም) ፤ እንዲያውም እጅግ በጣም ጭፍን ጥላቻ ነው። ፕሉምበር እና ኤሪክ (2006) 14 ብሄርን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች እና 4 ብሄር ተኮር ያልሆኑ ግጭቶችን በገመገመው ጥናታቸው ባልተረጋጉ መንግስታት ውስጥ ማንኛውም የብሄር ግጭቶች እና ጦርነቶች ሴቶችን ከወንዶች በበለጠ እንደሚጎዱ አረጋግጠዋል (ፕሉምበር እናኤሪክ ፣ 2020 ፤ ጆርጅ ፣ 2021)።

ኢትዮጵያም ከዚህ የተለየች አይደለችም። የመጀመሪያው የወረርሽኙ ተጠቂ በመጋቢት 2012 ዓ.ም ከተረጋገጠ በኋላ ፣ ኢትዮጵያ በኮቪድ-19 ዘርፈ ብዙ ተፅዕኖዎች ስትሰቃይ ቆይታለች።

ወረርሽኙ ያስከተለው የአደጋ ጊዜ የእንቅስቃሴ ገደብ የክልሎችን የህዝብ ትራንስፖርት እና የህዝብ መሰብሰቢያ መከልከል በሌላ በኩል የህዝቡን ኑሮ ጎድቷል። ከዚህም በላይ ወረርሽኙ ጾታን እንደማይለይ (ከሥርዓተ-ፆታ ገለልተኛ እንዳልሆነ) በብዙ ጥናቶች ተረጋግጧል። ሴቶቹን ለተጨማሪ ተግዳሮቶች እንደ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ፣ ብዝበዛ እና በደል ፣ የጤና እንክብካቤን እንደ እርግዝና ምርመራዎች ፣ የወሲብ እና የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች ተደራሽነት መቀነስ ፣ አነስተኛ የፖለቲካ ተሳትፎ እና ሌሎች የስነ-ልቦና ችግሮች አጋልጧል። (UN Women ፣ 2020 ፤ ገብረዋህድ እና ሌሎች ፤ 2020 ፡ አጃዪ እና ሌሎች 2020 ፡ ውድ እና ሌሎች 2021፡ ክርስቲያን እና ሌሎች፣ 2020፡ አሌሳንድራ ፣ 2020)።

በተመሳሳይ ከህዳር 11 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ኢትዮጵያ በፌደራል መንግስት እና በህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) መካከል በተፈጠረው ከፍተኛ ግጭት ስትሰቃይ ቆይታለች። ግጭቱ እንደአፋር ፣ አማራ እና ትግራይ ክልላዊ መንግስታት ከፍተኛ መጠን ያለው ሞት እና መፈናቀልን ጨምሮ የተለያዩ ሰብአዊ ቀውሶችን አስከትሏል (ሎረን ፣ 2021)። እንዲሁም በመንግስት ሃይሎች እና በታጣቂ ሃይሎች በተለይም በኦሮሞ ነጻነት ግንባር መካከል የተካሄዱ ተደጋጋሚ ግጭቶች በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት እየደረሰ ያለውን ሞት እና መፈናቀል የበለጠ አባብሶታል። ግጭቱ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የነካ ቢሆንም በግጭቱ ወቅት ሴቶች ጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ነበሩ። ግጭቱ በሴቶች ላይ በሚያደርሰው አካላዊ ፣ ወሲባዊ ፣ ስነ-ልቦናዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቃት በሴቶች ላይ ያልተመጣጠነ ተጽእኖ አስከትሏል (SRSG፣ 2021: RHINGO፣ 2021)።

ምንም እንኳን በግጭት በተጋለጡ አካባቢዎች ኮቪድ-19 እና ግጭቶች በሴቶች ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጉዳዮች ላይ (UN Women ፣ 2020 ፤ ገብረዋህድ እና ሌሎች ፣ 2020) የሚያስከትሉት ተጽእኖ ላይ የተደረጉ ብዙ ጥናቶች ቢኖሩም: አጃዪ እና ሌሎች 2020፡ ውድ እና ሌሎች 2021፡

ክርስቲያን እና ሌሎች ፣ 2020 ፡ አሌሳንድራ ፣ 2020) ፤ የኮቪድ-19 እና ግጭቶች ተፅእኖ በአጠቃላይ በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ በተለይም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ዙሪያ የተካሔዱ ጥናቶችና የተገኙ ግኝቶች ብዙ አይደሉም። ስለዚህ የጥናቱ ዓላማ ኮቪድ-19 በኢትዮጵያ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያደርሰውን ተፅእኖ ለመገምገም ሲሆን በአማራ ፣ አፋር እና ኦሮሚያ ክልሎች ለግጭቶች የሚያጋልጡ አካባቢዎችን እንደ ጥናት ወሰን አድርጎ በመውሰድ የተሰራ ነው።

# 3. የጥናቱ ዓላማዎች

የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ ኮቪድ-19 እና ግጭቶች በኢትዮጵያ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያደርሱትን ተጽእኖ ለመተንተን ሲሆን ይህም ግጭት በተከሰተባቸው እንደ አማራ ፣ አፋር እና ኦሮሚያ ክልሎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።

- ከግጭት በፊትም ሆነ በድህረ-ግጭት ሂደቶች በአማራ ፣ አፋር እና ኦሮሚያ ክልላዊ መንግስታት ላይ በማተኮር በኢትዮጵያ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ሁኔታዎች በጥልቀት ለመመርመር ፤
- ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች ፣ በአማራ ፣ አፋር እና ኦሮሚያ ክልላዊ መንግስታት ላይ በማተኮር ግጭት በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ (አቅም ፣ ደህንነት እና እንቅስቃሴ) ላይ የሚያደርሰውን ተፅእኖ ለመተንተን ፤
- በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ሒደቶችና ስራዎች የሴቶችን ተሳትፎ ሚና እና ተግዳሮቶች ለመተንተን።

# 4. የጥናቱ ዘዴ

## 4.1. የጥናቱ አቀራረብ

ጥናቱ መረጃን ለመሰብሰብ ፣ ለመገልበጥ እና ለመተንተን ኳሊቴቲቭ/ጥራትን መሰረት ያደረገ አቀራረብን የተጠቀመ ሲሆን በመጨረሻም በኤን.ዲ.አይ የጾታ እና ዲሞክራሲ የአሰራር ማዕቀፍ መሰረት ተቀርጿል።

## 4.2. የመረጃ ምንጮች

ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል። ዋና መረጃው የተሰበሰበው በትኩረት ቡድን ውይይቶች እና በቁልፍ መረጃ ሰጪ ቃለ-መጠይቆች ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ መረጃው የተሰበሰበው ደግሞ በተለያዩ የታተሙ እና ያልታተሙ ምንጮች (የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይቶች) ነው።

## 4.3. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

ጥናቱ የተለያዩ አሳታፊ ጥራት ያላቸው የመረጃ አሰባሰብና አቀራረቦችን እንዲሁም ከጥናቱ ዓላማዎች ጋር የተጣጣሙ ዘዴዎችን ተጠቅሟል። ከተለያዩ ተቋማት ጋር ውይይቶችን በማካሔድ ቀጥተኛ ኢንተርቪውና የተመረጡ ተወያዮችን ያሳተፈ የትኩረት ቡድን ውይይት (FGDs) በማድረግ በከፊል የተዋቀሩ ቸክ ሊስቶች ተዘጋጅተዋል። በአጠቃላይ የሚከተሉት አሳታፊ አቀራረቦች ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ ውለዋል፡-

- **የዴስክ ሪቪው፡-** የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን ለማረጋገጥ እና የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን በመጠቀም ሊሰበሰቡ የማይችሉ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አጥኚው የቡድን የዴስክ ሪቪው ዘዴዎችን ተጠቅሟል።
- **የትኩረት ቡድን ውይይት፡-** የትኩረት ቡድን ውይይቶች የተካሄዱት ይበልጥ ውስብስብ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አዳዲስ ሃሳቦችን ወይም አመለካከቶችን የሚሹ ፣ እንዲሁም የስርዓተ ጾታ ፣ የግጭት እና የፖለቲካ ተሳትፎ ተለዋዋጭነት ጋር የተያያዙ የተለያዩ አመለካከቶችን ለመረዳት ነው። ከተለያዩ የመንግስት ሴክተሮች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች የተውጣጡ ሴት ፖለቲከኞች በክልል ፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ ያሉ በውይይቱ ኢላማ ተደርገዋል/ ተካተዋል። በዚህም መሰረት በየክልሉ ሶስት የትኩረት ቡድን ውይይት የተካሔደ ሲሆን ከተለያዩ ቡድኖች የተውጣጡ ሴት ፖለቲከኞች በዋናነት በክልል ፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ ያሉ የመንግስት መዋቅሮች ተሳትፈዋል።

- **ጥልቅ ቃለ-መጠይቆች፡-** በፌዴራል ፣ በክልል ፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ ቁልፍ የመረጃ ሰጪዎች ጋር ቃለ ምልልስ ተካሂዷል። የሴቶች ፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ባለሙያዎች ፣ የገዥው ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላትና የስራ ኃላፊዎች ፣ የክልል ፣ የዞንና የወረዳ አመራሮች በጥናቱ ተሳታፊ ከነበሩት መካከል ናቸው።

### 4.4. የመረጃ ትንተና ዘዴ

መረጃው መጨረሻ ላይ በትክክል መተላለፉን ለማረጋገጥ ሁሉም ቁልፍ መረጃ ሰጪ ቃለ መጠይቆችና ከትኩረት ቡድን ውይይቱ የተሰበሰቡ መረጃዎች ተመዝግበው በጥንቃቄ በይለፍ ቃል ተቆልፈው ዩ.ኤስ.ቢ ስቲክ ላይ ከተቀመጡ በኋላ ብዙ ቃለ-መጠይቆች እና የትኩረት ቡድን ውይይቶች በመኖራቸው ረጅም ሂደት የነበረውን መረጃ በጽሁፍ የመገልበጥ/የማስፈር ስራ ተካሂዷል። በመጨረሻም ፣ ወደ ጽሁፍ ከተገለበጠ በኋላ ቴማቲካል ኮድ በመስጠትና መረጃውን በመልክ በመልኩ በማድረግ ተተንትኗል።

## 5. የጥናቱ አስፈላጊነት

ጥናቱ አምስት ቁልፍ ጠቀሜታዎች አሉት። በመጀመሪያ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር (ኢ.ሕ.ባ.ሴ.ማ) የጥናቱን ውጤት ተጠቅሞ በኤን.ዲ.አይ የተደገፈ ፕሮጀክት ለመተግበር እንደ መመሪያ ለመጠቀም ሞክሯል። በሁለተኛ ደረጃ ጥናቱ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት በማስረጃ የተደገፈ መረጃ በመስጠት ለፖሊሲ ማሻሻያ ጫና ለመፍጠር መሰረት ይጥላል። ሦስተኛ የዚህ ጥናት ግኝቶች ጠቃሚ ሲሆኑ ፖሊሲ አውጪዎች እና ፈጻሚዎች ክፍተቶቹን እንዲገነዘቡ እና የእርምት እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይረዳል። በመጨረሻም በዘርፉ ላይ ተጨማሪ ጥናትና ምርምር ለማድረግ ለሚፈልጉ ሰዎች እንደ መነሻ/ማጣቀሻ መሰረት ሆኖ ያገለግላል።

# 6. የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ዓላማ ኮቪድ-19 እና ግጭቶች በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ በሀገር አቀፍ ፣ በክልል ፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ ያደረሱትን ተፅእኖ ለመገምገም ሲሆን በመልክዓ ምድራዊ እና በቴማቲክ መልኩ የተቀረጸ ነው። መልክአ ምድራዊ አቀማመጥን መሰረት አድርጎ ጥናቱ በሶስት ክልሎች ማለትም በአማራ ፣ በአፋር እና በኦሮሚያ ክልሎች ብቻ በመወሰን የተካሔደ ነው። የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲሁም በክልል የመንግስት መዋቅር (በክልል ፣ በዞን እና በወረዳ) እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጨምሮ በብሔራዊ እና ክልላዊ መንግስት የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ አካቷል።

# ምዕራፍ ሁለት

## ግጭት ፣ ኮቪድ-19 እና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ በኢትዮጵያ

### 2.1. ቀውስ ፣ ስርዓተ ጾታ እና ዲሞክራሲ

እ.ኤ.አ. በ1979 በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀው እና እ.ኤ.አ በ1981 ሥራ ላይ የዋለው በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ማንኛውንም ዓይነት አድልዎ ማስወገድ ስምምነት (CEDAW) ከተፈረሙት የስምምነቱ ምሰሶዎች መካከል አንዱ በሕዝባዊ እና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የወንዶችና የሴቶች እኩል ተሳትፎ ነው። እ.ኤ.አ በ1995 በተመድ አራተኛው የዓለም የሴቶች ኮንፈረንስ የተዘጋጀው የቤጂንግ መግለጫ እና የድርጊት መርሀ-ግብር መድረክ በሁሉም ሀገራት ሴቶች በብሔራዊ ፓርላማዎች ውስጥ ካሉት ሁሉም ህግ አውጪዎች ቢያንስ 30% መሆናቸውን እንዲያረጋግጡ ጠይቋል። የአፍሪካ አጀንዳ እ.ኤ.አ 2063 አህጉሪቱ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ ያላትን ቁርጠኝነት ያፀደቀ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የሥርዓተ-ፆታ ክፍተቶችን በማሳየት ተጨባጭ መሻሻልን በማሳየት ረገድ ተጨባጭ መረጃ አስፈላጊ መሆኑን አምኗል። የማፑቶ ፕሮቶኮል የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚመለከቱ ልዩ አንቀጾችንም ያካተተ ሲሆን ይህም አህጉሪቱ በፖለቲካ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ የፆታ እኩልነትን ለማስፈን የረዥም ጊዜ ቁርጠኝነት መኖር እንዳለበት ያሳያል (IDEA፣ 2021)። በተቃራኒው ምንም እንኳን አፍሪካውያን ሴቶች በፖለቲካው ውስጥ ለመሳተፍ ቢሞክሩም የሀገራቸውን አካሄድ ለመለወጥ ብዙ ጊዜ አይሳካላቸውም ምክንያቱም ብዙ መሰናክሎች ስላጋጠሟቸው እና የፖለቲካ ምህዳሩ በተደጋጋሚ ለተሳትፏቸው ተስማሚ ስላልሆነ ነው (ኮውሬጅ ኤንድ ፎርጌት፣ 2019)።

ለምሳሌ፡- ሴቶች በአጭር እና በረዥም ጊዜ የችግር እና የቀውስ ውጤቶች ያልተመጣጠነ ተፅዕኖ ይደርስባቸዋል ፣ ከዚህ ጋር ተያይዞም ለጾታዊ ጥቃት እና ብዝበዛ የተጋለጡ ናቸው። በዚህም መገለል ፣ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ የሕሊና ጠባሳ እና ያልተፈለገ እርግዝና ፣ የሀብት አቅርቦት መቀነስ እና እኩል አለመሆን ፣ የኑሮ ግብአቶች ውስንነት ፣ መሰረታዊ አገልግሎቶችን መከልከል ፣ የቤተሰብ እና ማህበራዊ ሀላፊነቶች መጨመር ፣ የእንቅስቃሴ ገደቦች እና በዋነኛነት እንደ

ግጭት ባሉ ቀውሶች ወቅት በቂ የሆነ/የሚገባቸውን ያህል የፖለቲካ ስልጣን አለማግኘት የመሳሰሉት ችግሮች ይደርስባቸዋል። (USAID፣ 2009፣ አውድሬይ፣ 2014 ፣ ኮህን ፣ 2012)። የፖለቲካ ውዥንብር፣ የተራዘሙ የእርስ በርስ ጦርነት እና አለም አቀፍ ግጭቶች በተለይ በሴቶች እና በቤተሰቦቻቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሲያሳድሩ ይስተዋላሉ። በመሆኑም ቀደም ሲል በአባታዊ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉትን የሥርዓተ-ፆታ ክፍተቶች ያባብሳሉ (ፍቃዱ፣ 2020፤ ካምፕቤል እና ፓትሪሺያ 2005፤ ላርጅ፣ 1997)።

## 2.2. ቀውስ እና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ መቀነስ

ፕሉምበር እና ኤሪክ (2006) የኅሳ ጦርነቶች እና ግጭቶች ከወንዶች ይልቅ ሴቶችን በእጅጉ እንደሚጎዱ በ14 ብሄር ላይ የተመሰረቱ ግጭቶች እና 4 ብሄርን መሰረት ባላደረጉ ግጭቶች ላይ ባደረጉት ትንተና አሳይተዋል። የብሔር ግጭት ከሰብዓዊ ቀውስ ባሻገር በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል ይህም በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ያላቸውን ተጽእኖ ይቀንሳል (ሶንያ ፣ 2019 ፣ ኮህን ፣ 2012)። ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም (2020) እንደ ወረርሽኝ ፣ ግጭቶች፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ያሉ ቀውሶች በተከሰቱ ቁጥር በሁሉም ባለድርሻ አካላት የፖለቲካ ምህዳሩ እየቀነሰ መምጣት ይጀምራል ፣ ከዛም የፖለቲካ ስርዓቱ ከምክክር አሰራር ወደ ትዕዛዛዊ እና ቁጥጥር ሁኔታ አሰራር ይሸጋገራል። ቀውስ በሴቶች ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ከአካላዊ ችግር እና ከእውቀት ክፍተት አንፃር ብቻ ሳይሆን በፖለቲካዊ እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ ያላቸውን ስልጣን እና ድምጽ ከማጣት አንፃርም ጭምር መሆኑን ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም በግልፅ አሳይቷል። (ኤን.ዲ.አይ ፣ 2020)።

ደህንነቱ ያልተጠበቀ አካባቢ እና የእንቅስቃሴ ገደብ ፣ የመረጃ ፣ የግብአት እና የአገልግሎት አቅርቦት እጥረት እና መደበኛ ያልሆኑ ተቋማት የመረጃ መረቦች ቁጥጥር ያልተረጋገባቸውና ግጭት የተከሰተባቸው አካባቢዎች/ሁኔታዎች ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ለችግር ተጋላጭ ያደርጓቸዋል። (ካስቲሌጎ፣ 2011፤ ኮርዳኢድ፣ 2012፤ ኦኢሲዲ፣ 2013፣ UN Womesn፣ 2012፣ 2015)።

## 2.3. ኮቪድ-19 ፣ ግጭት እና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ በኢትዮጵያ

እንደ ሌሎች የዓለም ሀገራት ሁሉ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ሴቶች በህብረተሰቡ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የተገለሉ ሆነው ፣ መሰረታዊ ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ መብቶቻቸው ተነፍገው ኖረዋል። በኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች ፌዴራላዊ አወቃቀር የተመሰረተው እ.ኤ.አ በ1995 በወጣው ሕገመንግሥት ነው። በተጨማሪም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 35 ሴቶች የመምረጥና የመመረጥ መብት በማግኘት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ እኩል ዕድል ይሰጣል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 25 ሁሉም ህዝቦች በህግ ፊት እኩል መሆናቸውን ያረጋገጠ ሲሆን በፆታ ላይ የተመሰረተን ማንኛውንም አድልዎ ይከለክላል (የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት ፣ 1995)። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት በበለጠ ዝርዝር ሁኔታ ሴቶች በዚህ ሕገ መንግሥት የተሰጣቸውን መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። ሴቶች ሀገራዊ የልማት ፖሊሲዎች ሲዘጋጁ ፣ ፕሮጀክቶች ሲነደፉ እና ሲተገበሩ በተለይም የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ጉዳዮች ላይ ሙሉ በሙሉ የመመካከርና የመሳተፍ መብት አላቸው።

ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ወንዶችና ሴቶች እኩል መብት እንዳላቸው በግልጽ ቢያስቀምጥም ፣ አሁንም ሴቶች በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ፣ ድምጽና ተፅዕኖ እንዳይኖራቸው ጉልህ የሆኑ እንቅፋቶች ይስተዋላሉ። እነዚህ መሰናክሎች በስፋት የሚስተዋሉ ወሲባዊ እና ጾታ-ተኮር ጥቃት (SGBV) ፣ አሉታዊ ማህበራዊ አስተሳሰቦች እና የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች ፣ የተስፋፋ ግጭት እና አጠቃላይ የደህንነት ስጋትን ይፈጥራሉ (IRI እና NDI፣ 2021)። የሲቪል ማህበረሰቡ እና የፖለቲካው ዘርፍ አሰራር ግልጽ በሆነበት ወቅት የኢትዮጵያ ሴቶች አቋም እና ያሏቸው አማራጮች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለውጦችን አሳይተዋል። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት እየተካሔዱ ያሉ የብሔር እና የፖለቲካ ግጭቶች ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ፣ የአባታዊና ባህላዊ አስተሳሰቦች ሴቶች በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን እኩል እና ንቁ ተሳትፎ ማደናቀፋቸውን ቀጥለዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ በእጩነትም ሆነ በመራጭነት በጥቃትና ባለመረጋጋት ክፉኛ የተደናቀፈ መሆኑ በተደጋጋሚ ይገለጻል። በሴቶች ላይ የሚፈጸመው ጥቃት ቀጣይነት ያለው ጾታዊ ፣ አካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጥቃት ወይም በፖለቲካ ተሳትፏቸው ውስጥ የሚደርስ ትንኮሳ በማንኛውም ደረጃ ሊከሰት ይችላል። እነዚህ ባህሪያት በአጠቃላይ የሴቶች እምቅ አቅም ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራሉ ፣ በመሆኑም ለዲሞክራሲ መስፈን ስጋት ይፈጥራሉ። የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማበረታታት የተነደፉ የቅርብ ጊዜ የህግ እና ተቋማዊ ለውጦች ምንም እንኳን በተወሰነ መጠን ቢሆኑም (ለምሳሌ አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን ሴቶች በእጩነት ወይም በፓርቲ መሪነት ለሚያቀርቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተጨማሪ ድጎማ እንዲሁም ለፖለቲካ ፓርቲዎች ነፃ የአየር ሰአት መከፋፈሉ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ አበረታቷል (IRI እና NDI ፣ 2021 ፣ EWLA ፣ 2021)።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት ፣ የጠቅላይ ፍርድቤት ፕሬዝዳንት እና የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢን ጨምሮ የሴቶች ምርጫ እና ሹመትን በሚመለከት ሴቶች በህበረተሰቡ ውስጥ ሊጫወቱ የሚገባቸውን ወሳኝ ሚና እና የጾታ ተዋጽኦን አካታች የደረገ የፖለቲካ ስርዓት መሆኑን የሚያበረታታ ማሳያ ተደርጎ ተወስዷል። በይፋ እውቅና ከተሰጣቸው 53 የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል አንዱ ብቻ በሴት የሚመራ ሲሆን በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ 58 ሴቶች ብቻ የመሪነትን ቦታ ይይዛሉ። ምንም እንኳን ባለፈው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሴቶች ውክልና ከክልላዊ ጋር ሲነጻጸር (ከ24 በመቶ ወደ 39 በመቶ) ከፍ ያለ ቢሆንም ፤ ይህ ሊሆን የቻለው ኢህአዴግ ህጋዊ ያልሆነ የኮታ ሥርዓት ስለተጠቀመ ነው። በ2007 ዓ.ም 29 በመቶ የነበረው የሴት እጩዎች በመቶኛ እ.ኤ.አ በ2013 ዓ.ም ምርጫ ወደ 21 በመቶ ዝቅ ብሏል። ዋነኞቹ መንስኤዎች እጅግ በጣም ያልተረጋጋ የፀጥታ ሁኔታ ፣ የፀጥታ ስጋቶች ፣ ዛቻ እና ማስፈራራትን ጨምሮ በተለይ ሴት እጩዎች ተጋላጭ ናቸው። የኢኮኖሚ እጥረት እንዲሁም የተዛባና አድሏዊ የስርዓተ-ፆታ አመለካከት በሴቶች ህዝባዊ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ህይወት ላይ የበለጠ እንቅፋት ሆኗል (ኢ.ሕ.ባ.ሴ.ማ ፣ 2021 ፤ IRI እና NDI ፣ 2021)።

## 2.4. ግጭት እና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ

ግጭቶች በታሪክ ውስጥ በሴቶች ላይ ጭቆና ሲያስከትሉ ይታወቃሉ። ሴቶች ከወንዶች በበለጠ ለአሉታዊ ተጽእኖዎች የተጋለጡ ናቸው ፤ በተለይም በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ አደጋዎች ወቅት። ለምሳሌ:- SIDA (2015) እና (ጆርጅ ፣ 2021) ባደረጉት ጥናት ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ፣ የኑሮ ውድነቶች መከሰትና የሴቶች ከውሳኔ ሰጪነት መገለል የግጭት እና የድህረ ግጭት እንዲሁም የአለም አቀፍ ወረርሽኝ ውጤቶች መሆናቸውን አረጋግጠዋል። በተጨማሪም ግጭቶችና ወረርሽኞች በሴቶች ማኅበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነልቦናዊ ጉዳዮች ላይ ከተለመዱት ተጽእኖዎች ባሻገር የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ እንዴት እንደሚጎዱ የሚያሳዩ አዳዲስ ጥናቶች አሉ (ፋልክ ፣ 2010)። እንደ ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት ወረርሽኞች ፣ ግጭቶች እንዲሁም የተፈጥሮ እና ሰውሰራሽ አደጋዎች ያሉ ቀውሶች ሲከሰቱ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት የፖለቲካ ምህዳሩ እየጠበበ እና አጠቃላይ የፖለቲካ ስርዓቱ ከምክክር አሰራር ወደ ትዕዛዝ እና ቁጥጥር አሰራር (2020) ይቀየራል። በአካባቢያዊ ውስንነቶች ፣ በእውቀት ክፍተቶች እና በፖለቲካ እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ድምጽ በማጣት በተለይ ሴቶች ተጎጅ ሆነዋል (ኤን.ዲ.አይ ፣ 2020)።

በግጭት ወቅት ሴቶች እና ልጃገረዶች ከወንዶች በተለየ መልኩ ሃላፊነት ይሸከማሉ። በሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ የግጭት መዘዝ ሊባባስ የሚችለው ቀደም ሲል በነበረው የፆታ ልዩነት እና መድልዎ ምክንያት ሲሆን ድህነትና ሴትነት ሴቶች እነዚህን ተፅእኖዎች ለመቀነስ ያላቸውን አቅም ይገድባሉ። ለምሳሌ እንደ ሴቶች እና ህጻናት መረጃ በጦርነትና በግጭት ምክንያት ስደተኞች እና የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ከፍተኛውን የችግር ተጋላጭነት ድርሻ ይይዛሉ። ግጭቶች ሴቶችን ለከፍተኛ ወሲባዊና ጾታ-ተኮር ጥቃት (SGBV) ተጋላጭነት ይዳርጋሉ ፣ በትምህርት ቤቶች በመመዝገብና በመማር ላይ ያለውን የሥርዓተ-ፆታ ልዩነት ያሰፋሉ ፣ የስነ ተዋልዶ ጤና ጉዳዮችን ያዛባሉ ፣ ልጆችን የመውለድ እና እንክብካቤ የማድረግ ሚናዎች ላይ ስጋት ይፈጥራሉ (ዶሚንጎ እና ሆልሜስ ፣ 2013 ፤ ማይርቲኔን እና ሌሎች ፣ 2014 ፤ UN Womens ፣ 2015)።

በሌላ በኩል ሴቶችን ማብቃትና ተሳትፏቸውን ማጠናከር ዘላቂ ሰላምን ሊያረጋግጥ ከመቻሉም በላይ በሕገ መንግሥት ለውጥ እና በሰላም ውይይቶች ውስጥ የሴቶችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ ይጨምራል (OECD ፣ 2013 ፣ ፓፈንሆልዝ እና ሌሎች ፣ 2016 ፣ UN Women ፣ 2015)። ሴቶች በሰላም ድርድር ላይ ሲሳተፉ የሰላም ስምምነት ቢያንስ ለ15 ዓመታት ሊቀጥል የሚችልበት 35% የበለጠ እድል አለ። ስለዚህ ሴቶች በቤተሰብ ፣ በማህበረሰብ እና በሀገር ደረጃዎች ሰላምን ፣ ደህንነትን እና መረጋጋትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ (ካርዶና እናሌሎች ፣ 2012 ፤ ጆርጅ ታወን ኢንስቲትዩት ፣ 2015 ፤ UNSG ፣ 2010 ፤ UN Women ፣ 2015)። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ በተለይ በሰላም ግንባታ እና በግጭት አፈታት ሂደቶች ላይ ያሉ ጅምሮች የህብረተሰቡን ከፍተኛ ቁጥር ድርሻ የሚይዙ ሴቶችን ያገለሉ ሲሆኑ ከታሪክ መረዳት እንደሚቻለው ደግሞ ከግጭት አፈታት እና ከሰላም ግንባታጋር የተያያዙ እሴቶች ፣ ፖሊሲዎች ፣ ተቋማት እና አሠራሮች እጅግ በጣም ብዙ የሆነውን የህብረተሰብ ክፍል በተለይም ሴቶችን ያገለሉ ናቸው። (አግባጆቢ ፣ 2010)።

## 2.5. ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ እና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ


እ.ኤ.አ በታህሳስ ወር 2011 መጨረሻ ላይ በቻይና ሁቤይ ግዛት ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው ኮሮና ቫይረስ 2019 (ኮቪድ-19) ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሁሉም ሀገራት ወይም ክልሎች ተሰራጭቷል ፣ እ.ኤ.አ መስከረም 04 ቀን 2015 ዓ.ም የጤና ባለሙያዎች 607,083,820 የተረጋገጡ የCOVID-19 በሽታ ኬዞች መኖራቸውን አረጋግጠዋል ፣ ከእነዚህም መካከል 6,496,721 ሞት ለዓለም ጤና ድርጅት ሪፖርት ተደርጓል። ከመስከረም 02 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ 12,613,484,608 ክትባቶች ተሰጥተዋል (ቤልግሌይ ፣ 2020 ፤ CIM ፣ 2020 ፤ CARE ፣ 2020)። ቫይረሱ በፖለቲካ ምኅዳሩ ላይ በተለይም በሴቶች ላይ በርካታ መሰናክሎችን ፈጥሯል። በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ሴቶች እና ወንዶች እንደ የመራጮች ምዝገባ ፣ የእጩዎች ሹመት ፣ የመራጮች ትምህርት ፣ የምርጫ ቅስቀሳ እና ድምጽ አሰጣጥ በመሳሰሉት የፖለቲካ ሂደቶች ውስጥ በተሳካ ሁኔታ መሳተፍ አይችሉም ፣ በተለይም በበሽታው ከተያዙ ወይም በለይቶ ማቆያ ውስጥ ከሆኑ ማለት ነው።

ወረርሽኙ ቢከሰትም በ2020 በ18 የአፍሪካ ሀገራት ምርጫ ተካሂዶ የነበረ ሲሆን ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች አራት ሀገራት ምርጫቸውን ወደ ሌላ ጊዜ አራዝመዋል። ከዛም ከመጀመሪያው በበለጠ አህጉሪቱን በከፍተኛ ደረጃ እያወደመ ባለው በሁለተኛው ወረርሽኝ ጊዜ ፣ በ2013 ዓ.ም 26 ምርጫዎች እንዲካሄዱ ተወሰነ (ፑናም ፣ 2021 ፤ IDEA ፣ 2021)።

እንደ ኮቪድ-19 እና አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ያሉ ቀውሶች ከስርዓተ-ፆታ አድሎ የጸዱ አልነበሩም። ሴቶቹን ለተጨማሪ ችግሮች እንደ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ፣ ብዝበዛ እና በደል ፣ ለጾታዊ እና ስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተደራሽነት መቀነስ ፣ የጤና-አገልግሎት እንደ ቅድመ ወሊድ አገልግሎት ማጣት ያሉ ፈተናዎች እና ሌሎች ስነ-ልቦናዊ ጉዳቶች አጋልጧል። በተጨማሪም የሴቶችን የፖለቲካ ስልጣን እና የመንቀሳቀስ ነፃነት ተደራሽነት ገድቧል (UN Women ፣ 2020 ፤ ገብረዋህድ እና ሌሎች ፣ 2020 ፤ አጄይ እና ሌሎች ፣ 2020 ፤ ውድ እና ሌሎች ፣ 2021 ፤ ክርስቲያን እና ሌሎች ፣ 2020 ፤ አሌሳንድራ ፣ 2020)። ቀውሱን ለመቅረፍ በፓርላማ ውስጥ በተቋቋሙት የውሳኔ ሰጪ እና ቁጥጥር ኮሚቴዎች/ግብረ ሃይሎች ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ እና አመራራቸውን ማረጋገጥ ወሳኝ ነው (ቤልግሌይ ፣ 2020 ፤ CIM ፣ 2020 ፤ CARE ፣ 2020 ፤ ፑናም ፣ 2021 ፤ IDEA ፣ 2021)። ለምሳሌ ፣ በኮቪድ-19 ፣ ፓርላማዎች የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን በማሳካት ረገድ ወሳኝ ተግባራቸውን መወጣታቸውን ለማረጋገጥ አዳዲስ የአሰራር ስልቶችና ሂደቶች ያስፈልጋሉ። ፓርላማዎች ምርጫ እንዲያካሂዱና ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ እና የኮቪድ-19 ጉዳዮችን የሚያንፀባርቁ እርምጃዎችን እንዲወስዱ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት አስፈላጊ ነው። ቀውሱ ፓርላማዎች ለሥርዓተ-ፆታ ትኩረት የሚሰጡ ተቋማት ሆነው እንዲቀጥሉ መልካም ዕድል የፈጠረ ነው (IDEA፣ 2021፣ IPU እና UN Women፣ 2021)። ሴቶች ለኮቪድ-19 የማገገሚያ ማዕከላት ማስፋፊያ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ መሆን አለባቸው ፣ ይህ ሂደት የሚጀምረው በእኩል ውክልና እና በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ መካተታቸውን በማረጋገጥ ነው። እንደ ስርዓት ኮታ ያሉ አካሔዶች ተሳትፏቸውን ለማረጋገጥ ልዩ እርምጃዎችን ቢወስድም ሴቶች በኮቪድ-19 ልዩ ቡድኖች ወይም ግብረ ሃይሎች እንዲሁም በሕግ አውጪ ፣ ፖሊሲ እና የበጀት ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች

ውስጥ መካተት አለባቸው (UN Women ፣ 2020 ፤ OCHA ፣ 2020 ፤ ጁሊያ ፤ 2020)።

ወረርሽኞች ፣ ግጭቶች ፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በሴቶች ማህበራዊ ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ላይ የሚያደርሱትን ተፅእኖ ለመለካት ከመደበኛው አሰራር በተጨማሪ ግጭት እና ወረርሽኞች ሴቶች ትርጉም ያለው የፖለቲካ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው እንዴት እንደሚያግዷቸው ማጣራት ያስፈልጋል (ራቻርድ ፣ 2021)። የሚከተለው ሥዕላዊ መግለጫ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም (2020) በቀውስ ፣ በዲሞክራሲ እና በጾታ እኩልነት መካከል ያለውን የመስተጋብር ማዕቀፍ እና ስጋት እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ እንዴት እንደሚጎዳ እና እንደሚነካ ያሳያል።




**ምንጭ:- ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም : 2020**

## 2.6. ግጭት እና ኮቪድ-19 በኢትዮጵያ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ያሳደሩት ተጽዕኖ - ከአፋር ፣ ኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ኬዞችን በመውሰድ የተደረገ ጥናት

እንደ ወረርሽኞች ፣ ግጭቶች ፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ያሉ ቀውሶች የሁሉም ባለድርሻ አካላትን የፖለቲካ ምህዳር በማጥበብ የምክክር አሰራሮችን የበለጠ ወደ ትዕዛዝና ቁጥጥር ስርዓት ይቀይራሉ። ይህ የምህዳር መጥበብ በዋነኛነት ለሴቶች አስጨናቂ ነው ምክንያቱም በቦታ ውስንነቶች እና በእውቀት ክፍተቶች እንዲሁም በፖለቲካ እና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ድምፃቸውን እና ውክልናቸውን ያሳጣቸዋል (NDI ፣ 2020)። በመሆኑም ሴቶች በማደግ ላይ ባሉ እና ባደጉ ሀገራት በተከሰቱት አደጋዎች ያልተመጣጠነ ጉዳት ይደርስባቸዋል። በማህበራዊ ኢፍትሃዊነት እና በፆታ እኩልነት አለመመጣጠን ምክንያት ለአደጋ የተጋለጡ እና እራሳቸውን ለመከላከል አቅም የሌላቸው ናቸው (SIDA ፣ 2009)። እነዚህ ቀውሶች ብዙውን ጊዜ እኩልነት እንዳይረጋገጥ በማድረግ ነገሮችን ያባብሳሉ። ምንም እንኳን ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የቀውስ ጊዜ ችግሮችን ማለፊያ መንገዶች ላይ በሚኖራቸው አፈጻጸም ዕውቅና የሚያገኙ ብዙ ሴት አመራሮች ቢኖሩም በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች ውስጥ ግን ሴቶች አሁንም ችላ ይባላሉ። ተመራጭ ሴት ባለስልጣናት ፣ ሴት እጩዎች እና ሴት መራጮች በተለይ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና በቀጣይ ጉዳቱ በሚያስከትለው ያልተመጣጠነ የጾታ እኩልነትን በሚያባብሱ እና መሰናክሎችን በሚያጠናክሩ ተጽዕኖዎች ተጎጂዎች ናቸው (IDEA ፣ 2022)።

ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ወንድና ሴት እኩል መብት እንዳላቸው በግልጽ ቢደነግግም ትርጉም ያለው የፖለቲካ ተሳትፎን ጨምሮ ሴቶች በኅብረተሰቡና በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ እኩልና ንቁ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው ከፍተኛ እንቅፋቶች አሉ። እነዚህ መሰናክሎች ዘላቂ የአባታዊ ባህልና አስተሳሰቦች ፣ የብሔር እና የፖለቲካ ግጭቶች ፣ ጎጂ ልማዶችና የተዛቡ የማህበረሰብ አመለካከቶች እንዲሁም የተዛቡ የስርዓተ-ፆታ ሚናዎች ፣ ጾታዊ እና ጾታ ተኮር ጥቃቶችን ያካትታሉ (CEPPS ፣ 2020 ፣ EWLA ፣ 2021 ፣ IRI እና NDI ፣ 2021)። ሁከት እና የጸጥታ መደፍረስ እንደ ድምጽ አሰጣጥ እና የምርጫ ውድድር ባሉ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ሂደቶች ላይ ትልቅ እንቅፋት

እንደሚፈጥሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ ይታወቃል (IRI እና NDI ፣ 2021 ፣ EWLA ፣ 2021 ኮህን፣ 2012)።

ግጭት እና ኮቪድ-19 በሴቶች ላይ በሚያደርሱት ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነ-ልቦናዊ ተፅእኖና  ቀውስ ላይ ብዙ ጥናቶች ቢደረጉም በአጠቃላይ በዓለም በተለይ በኢትዮጵያ በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ በሚያደርሱት ተጽዕኖ ላይ የተደረጉ ጥናቶች ግን ጥቂት ናቸው። (UN Women ፣ 2020 ፣ ገብረዋህድ እና ሌሎች ፣ 2020 ፣ አጃዬ እና ሌሎች ፣ 2020 ፣ ውድ እና ሌሎች ፣ 2021 ፣ ክርስቲያን እና ሌሎች ፣ 2020 ፣ አሌሳንድራ ፣ 2020)። ስለዚህ የጥናቱ ዋና ዓላማም ግጭት የተከሰተባቸውን የአማራ ፣ የአፋር እና የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስታት እንደ ጥናት አካባቢ በመውሰድ ኮቪድ-19 እና ግጭቶች በኢትዮጵያ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅእኖ ለመገምገም ነው። እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 ያሉ አስደንጋጭ ተፅእኖዎችን ለመለካት የተለያዩ መንገዶች አሉ። ለምሳሌ:- ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት (2020) ቀውስ በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ለመለካት አራት መንገዶችን ዘርዝሯል። እነዚህም የተዛቡ አመለካከቶች ፣ የመረጃ ክፍተት ፣ ድምጽ እና አካላዊ ጉዳቶች/ስጋቶች ናቸው። በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ላይ በመመስረት በተሰበሰቡ መረጃዎች መሰረት ግጭት እና ኮቪድ-19 በኢትዮጵያ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ያደረሷቸዉ ዋና ዋና ተፅዕኖዎች የሚከተሉት ናቸው።

**የሚከተለው ሥዕላዊ መግለጫ በጥናቱ የተገኙትን ተፅዕኖዎች ማጠቃለያ ያሳያል:-**




**መረጃው የተወሰደው በጥናትና ምርምር ቡድን ፣ በ2014/15 ዓ.ም ነው**

ተፅዕኖዎቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡-

1) **የደህንነት ስጋት እንደ ሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት፡-** እንደ ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት ቤት የሀገራዊ ደህንነት ስራ በአለም አቀፍ ደረጃ ከሚሰራ ይልቅ በፖለቲከኞች እና በሌሎች ውሳኔ ሰጪዎች በጥንቃቄ ቢሰራ ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም ማህበራዊ እና ተቋማዊ ብቃት ያለው “የደህንነት አካል በአብዛኛው ፖለቲካዊ ጉዳዮችን “ከፖለቲካ ፍጆታ ባለፈ” እንደ “አደገኛ” ፣ “አስጊ” ፣ “አሳሳቢ” ፣ “አስፈሪ” እና የመሳሰሉትን አድርጎ ይቆጥራቸዋል (ስቴፈን 2017)፡፡ የደህንነት አካላት ጉዳዮችን በቁም ነገር በመመልከት "ቅድሚያ" የመስጠት ወይም የማቃለል እና ችላ የማለት ምርጫ አላቸው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ፣ ግጭትም ሆነ ኮቪድ-19 በአገር ውስጥና በአካባቢ ደረጃ ችግር ሲፈጠር በአብዛኛው የማህበረሰብ እና የፖለቲካ መሪዎች ሁኔታዎች ከባድ እና አስቸኳይ መሆናቸውን እና ለእነሱ ትኩረት መስጠት ወይም ችላ መባል እንዳለበት የሚወስኑት “የደህንነት አካላት” ናቸው፡፡ ይህ የሀገርን ገጽታ መጠበቅ ወይም በሴቶች እና በሌሎች የተገለሉ ቡድኖች ዘንድ የደህንነት እጦት ሲባባስ የጦር መሳሪያን በዲሞክራሲያዊ መልክ መጠቀም ተብሎ ተገልጿል (የአለም ባንክ ፣ 2018)፡፡ ጥናቱ በተካሔደባቸው አካባቢዎች ለሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት የሆኑ የአካባቢው ደህንነት/የጸጥታ ሁኔታ በሶስት መልክ ተገልጿል፡- እነሱም የተቋም ፣ የቤት ውስጥ እና የግል ደህንነትን ማስጠበቅ ናቸው፡፡

· **የተቋም ደህንነት ስጋት እንደ ሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት፡-** ችግሩን ለመቅረፍ እና “አደገኛ” ፣ “አስጊ” ፣ “አሳሳቢ” ወይም “አስደንጋጭ” ለማለት የፖለቲካ ፓርቲዎች ፣ የመንግስት አካላት እና ማህበራዊ አደረጃጀቶች ከማህበራዊ እና ተቋማዊ ባለስልጣናት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በጥናቱ የተሳተፉት ወንድ አመራሮች በእነዚህ ድርጅቶች ላይ የበላይ እንደሆኑ ተናግረዋል፡፡ በመሆኑም “አስጊ” ፣ “አደገኛ” ፣ “አሳሳቢ” እና “አስደንጋጭ” ተብሎ የሚፈረጅ ወንድ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያስተሳሰረ ሲሆን እነዚህ ኃይሎችም ለችግሩ መፍትሄ ይሰጣሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት በኦሮሚያ ፣ አፋር እና አማራ ክልሎች የተካሄዱት የቁልፍ ጥያቄ ምላሾች እና የትኩረት ቡድን ውይይቶች በክልል ፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ የተዋቀሩ ተቋማዊ እና ማህበራዊ

ባለስልጣናትን ግጭትን መሰረተ አድርጎ ለሚከሰት የቀውስ ደረጃ የመጀመሪያ ደረጃ ሃላፊነት አለባቸው ብለዋል። በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ወንዶች የበላይ ስለሆኑ ደህንነትን የሚገልጹት ከራሳቸው አመለካከት/እይታ አንጻር ነው። ወንዶች በግጭት ጊዜ ሁኔታውን ይከታተላሉ ፣ የሴቶችን የውሳኔ አሰጣጥ አይነት እና የተሳትፎ መጠን ይወስናሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ አመራሮች በአብዛኛው ወንዶች ሆነው ሁኔታውን ለመምራት እና ሴቶቹ ቤተሰቦቻቸውን እንዲንከባከቡ ወይም በቁሳቁስ እና በሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት መስኮች ተሰማርተው ተጨማሪ ሚናዎችን እንዲጫወቱ ለማሳመን ይወስናሉ፡፡ በአማራ ክልል ምዕራብ ወሎ ዞን የቁልፍ ምላሽ ሰጪ ጥያቄዎች መረጃ ሰጪዎች አንዷ እንዲህ ብለዋል:-

> “ባለሥልጣኖቻችን ሁል ጊዜ በችግር ጊዜ ወደቤታችን እንድንመለስ ወይም ነገሮችን የማመቻቸት ሚናዎችን እና የቁሳቁስ ተኮር አቅርቦት ሥራዎችን እንድንሠራ ይመክሩናል። እኛ የካቢኔ አባላት ብንሆንም ምን ማድረግ እንዳለብን እና እንዴት ማከናወን እንዳለብን ምክር አይጠይቁንም።ከበስተጀርባ ያሉት ምክንያቶች የኛን ደህንነት ለመጠበቅ ይሁን ወይም የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ እርግጠኛ አይደለንም ፣ በመሆኑም በአብዛኛው የግጭት ሁኔታዎችን በሚያካትቱ ቀውሶች አያያዝ ላይ እንድንሳተፍ አይፈልጉም። ስለዚህ የእኛ ሚናዎች የድጋፍ አገልግሎቶችን መስጠት ወይም ለጥበቃ ወደ ቤት መመለስ ናቸው”

በአጠቃላይ ይህ ሁኔታ ወንድ መሪዎቹ እንደ ኮቪድ-19 እና ግጭት ያሉ ቀውሶች ሲፈጠሩ ለመቆጣጠር ዕድሉን ተጠቅመው ሁሉንም የውሳኔ ሰጪነት ቦታዎች እንደሚቆጣጠሩ ይጠቁማል። በሌላ በኩል ይህ በቅድመ ግጭት ፣ በግጭት እና በድህረ-ግጭት ወቅቶች በአብዛኛው በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ተጽእኖ ነበረው። በኮቪድ-19 የእንቅስቃሴ ገደብ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የሴቶችን እንቅስቃሴ እና የፖለቲካ ተሳትፎ ለመጠበቅ እና ለመገደብ በተቋማት እና በማህበረሰቡ መካከል ያሉ ሃይሎች ተመሳሳይ ሂደቶችን ተጠቅመዋል። ይህ የደህንነት ጥበቃ ለኮቪድ-19 ሰፊ የሚዲያ ሽፋን በመስጠት ፣ በወንዶች የበላይነት የሚመሩ አጫጭር የሚዲያ መግለጫዎች እና ምርጫን ጨምሮ የበርካታ የፖለቲካ ሁነቶች መጓተትና ሴቶች ለፖለቲካ እንቅስቃሴ በሚያደርጉት የስነ-ልቦና ዝግጅት ላይ ተጽእኖ አሳድሯል። ከኦሮሚያ ክልል የጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል አንዷ እንዲህ ብለዋል:-

ወረርሽኙ ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ሁሉም መሪዎቻችን ወደ ሀገር ቤት ሊልኩን በጣም አጓጉተውናል። በተጨማሪም ኮቪድ-19 ከወንዶች ላይ ይልቅ በሴቶች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አለው በማለት አስጨንቀውናል። ሀዘኔታቸውንም ገልጸውልናል ፣ በዚህም ደስ ብሎናል ፣ እናም ወደ ቤታችን ተመለስን፡፡ እንደ መልካም እድል አይተነው መቆየትን መረጥን ፤ ነገር ግን ወንድ አቻዎቻችን ሁኔታውን ተጠቅመው ከፋይናንስ ፣ ከእውቀት እና ከሌሎች ተቋማዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ሁኔታዎችን ተቆጣጠሩ/አላግባብ ተጠቀሙ፡፡

በውጤቱም ፣ እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 ያሉ ሁኔታዎችን የሚገልጹ ቃላቶችን በመጠቀም ቀውስን የሚያባብስ ሰው የተደረገውን ምርጫ እና የተገኘውን ውጤት እንደሚቆጣጠር ተደርሶበታል ፤ እነዚህ አሰራሮች ደግሞ የሴቶችንና የሌሎች ግለሰቦችን ተሳትፎ ይገድባሉ። ይህ አሰራር በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ በተለይም እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 ባሉ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ተሳትፎ በአስደንጋጭ ሁኔታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲሆን ተጽዕኖ አሳድሯል።

- **የቤት ውስጥ ደህንነት ስጋት እንደ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት፡-**

ይህ ሁኔታ ከላይ ከተጠቀሰው ሁኔታ በተመሳሳይ መልኩ ወንዶች በተለይም ባሎች የትዳር ጓደኞቻቸው እንደ ኮቪድ-19 ባሉ ቀውሶች ጊዜ የፖለቲካ እና የአካባቢ ግጭቶች ላይ የሚኖሩ እንቅስቃሴዎችንም ሆነ የህዝቡን ህይወት ደህንነት እንዲመሩ አይፈልጉም። ይህንን መከራከሪያ ሃሳብ ለመደገፍ መረጃ ሰጪዎቹ በሁለት መንገዶች ይገልጻሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ባሎች ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ጦርነት እና ኮቪድ-19ን ጨምሮ ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው ብለው ያስባሉ። በሁለተኛ ደረጃ እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 ባሉ ቀውሶች ጊዜ ሴቶች ቤተሰብን ከመንከባከብ አንፃር ከማንም በላይ ከባድ ሸክም ይሸከማሉ። በዚህ ምክንያት ፣ እንደ ኮቪድ-19 እና ግጭቶች ወይም በጤና ላይ የሚደርሱ ድንገተኛ አደጋዎች በተከሰቱ ጊዜ ባሎች ሁኔታውን በመከታተል ሚስቶቻቸውን በቤት ውስጥ እንዲቆዩ ያሳምኗቸዋል ፤ ይህም ሴቶች በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ በተለይም በፖለቲካ ውስጥ እንዳይሳተፉ ቀጥተኛ ተጽእኖ ይኖረዋል። በምዕራብ ወለጋ ከነበሩት መረጃ ሰጪዎች አንዷ እንዲህ ብለዋል:-

"በዚህ አካባቢ የካቢኔ አባል መሆን ወይም ሌላ ማንኛውንም የአመራርነት ቦታ ለመያዝ የታጠቁ ሀይሎች ወደሚንቀሳቀሱባቸው አደገኛ ገጠራማ አካባቢዎች መሄድን ይጠይቃል። ከሥራ ጋር በተያያዘ ወይም አካባቢውን በማደራጀት ከታጠቁ ሀይሎች ለመጠበቅ ሊሆን ይችላል።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ባሎች የታጠቁ ቡድኖች በትዳር ጓደኞቻቸው ላይ ጥቃት ሊሰነዝሩ ይችላሉ ብለው ስለሚጨነቁ ቁጥጥር ያደርጋሉ። በዚህ ምክንያት ከቤት ውስጥ ሆኖ መሥራት እየከበደ ስለሚመጣ ሰዎች ሥራቸውን የሚያቋርጡበት አዝማሚያ እያደገ ነው።"

ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው መላሾችም ባሎቻቸው በኮቪድ-19 ወቅትም ተመሳሳይ ስልት እንደሚጠቀሙ አረጋግጠዋል። ባለትዳሮች ሚስቶቻቸውን በማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች/ጉዳዮች ላይ እንዳይገኙ ያሳምኗቸዋል። በአፋር ከሚገኙ መረጃ ሰጪዎች መካከል አንዷ እንዲህ ብለዋል፦

"ባሎቻችን ኮቪድ-19 ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በስብሰባዎች ፣ በውይይቶች እና በማንኛውም የፖለቲካ ተሳትፎ መሳተፍን ጨምሮ በህዝቡ ውስጥ ባለን የህይወት እንቅስቃሴና ተሳትፎ ላይ ገደብ ማድረግ ጀመሩ። ሚስቶች ከወንዶች በበለጠ በወረርሽኙ ሊያዙ እንደሚችሉ እና ወደ ባሎች እና ልጆችም ያሰራጫሉ ብለው ያስባሉ።"

ወንዶች ሁሉንም በህዝቡ የዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን እንደሚቆጣጠሩ እና ሴቶቹ በቤት ውስጥ እንዲቆዩ እንደሚያስገድዱ ይህም በተለይ በምርጫ ወቅት የሴቶችን ተሳትፎ በመገደብ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል" በማለት ይከራከራሉ።

ከአፋር ተሳታፊዎች መካከል አንዷ በበኩላቸው እንዲህ ብለዋል፦

"ኮቪድ-19 ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ባሎቻችን በስብሰባዎች ፣ ዝግጅቶች እና በፖለቲካ ተሳትፎ ላይ መገኘትን ጨምሮ በህዝቡ ህይወት ውስጥ ያለንን ተሳትፎ መገደብ ጀምረዋል። ሚስቶች ከወንዶች በበለጠ በወረርሽኙ ሊያዙ እንደሚችሉ እና ወደ ባሎች እና ልጆችም ያሰራጫሉ ብለው ያስባሉ። በህዝቡ የእለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ያሉ ሁሉንም ጉዳዮች እነሱ ተረክበው እኛ ቤት እንድንቆይ ያስገድዱናል ፤ ይህም በተለይ በምርጫ ወቅት በሚኖረን ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል" በማለት ይሟገታሉ።

- **የግል ደህንነት ስጋት እንደ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት፦**

ሴቶች እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 ባሉ አስደንጋጭ ሁኔታዎች ውስጥ አስተማማኝ ጥበቃ እና ደህንነት እንዲሰማቸው ስለሚፈልጉ ከፖለቲካ የመራቅ አዝማሚያ ያሳያሉ። መረጃ ሰጭዎቹ እንዳሉት ሴቶች ፈተናዎችን እና ግጭቶችን ጤናማና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ለመጋፈጥ እንደሚፈልጉ ገልጸዋል። ሴቶች በፖለቲካ እና በሌሎች ህዝባዊ ጉዳዮች ላይ ከመሳተፍ ይልቅ ለግል ደህንነት ቅድሚያ ይሰጣሉ። ይህም ከወንዶች ቤተሰብ የመጠበቅ እና የመንከባከብ ዝንባሌ ጋር ይቃረናል።

ሴቶቹ ለደህንነታቸው ቅድሚያ ይሰጣሉ በመሆኑም በቤት ውስጥ ወይም በሥራ ቦታ የወንዶች ተጽእኖ በሚኖርበት ጊዜ ቤት ውስጥ በመቆየት የግል ደህንነታቸው የአስተማማኝነት ሁኔታ ላይ ያላቸውን ጥርጣሬ ያስወግዳሉ፡፡ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ከመጡ መረጃ ሰጪዎች መካከል አንዷ እንዲህ ብለዋል፡-

"ከታጣቂዎች ጋር ያለህ ግንኙነት እና ግጭት በኃላፊነትህ እና በሙያህ እድገት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል። ራቅ ወዳሉ ክልሎችና የታጠቁ ሀይሎች ወደሚንቀሳቀሱበት አካባቢ መሄድ አለብህ። በዚህም ግጭት ውስጥ ላለመግባት ወደ አካባቢው ለመጓዝ እንሰጋለን። ከዛም ወንዶቹ አጋጣሚውን በመጠቀም እያንዳንዱን ጉዳይ /እንቅስቃሴያችንን ይቆጣጠራሉ፡፡"

በመንግስት ሴክተሮች ከሚሰነዘረው የደህንነት ስጋት በተጨማሪ በሀገሪቱ ያለው አጠቃላይ የጸጥታ ችግር እና በተለይ ለግጭት በተጋለጡ አካባቢዎች በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ተጽእኖ ማሳደሩን ከተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የመጡ ሴቶች አረጋግጠዋል፡፡

**2) ማስፈራራት** ለሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት፡-

ሴት ፖለቲከኞች (የፖለቲካ ፓርቲ እጩዎችም ሆኑ የመንግስት ካቢኔዎች) የታጠቁ ቡድኖች በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች በተለይ በኦሮሚያ ፣ በአማራና በአፋር ክልሎች በፖለቲካው መስክ በንቃት ለመሳተፍ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ በጥናቱ ተረጋግጧል። ምክንያቱም የታጠቁት ቡድኖች ፖለቲከኞች በዋነኛነት ሴቶች በዞንና በወረዳ ከፍተኛ ኃላፊነት ላይ እንዳይወጡ ለማድረግ ስነ ልቦናዊ እና አካላዊ ማስፈራራትን ይጠቀማሉ። ሴቶችን ለማስጠንቀቅ እና ጭንቀትን ለመፍጠር የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። እነዚህ ማስፈራሪያዎች ሰዎች መኖሪያቸውን እንዲቀይሩ እና ከስልጣናቸው እንዲለቁ ያደርጓቸዋል፡፡ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ ዞን ከመጡ መረጃ ሰጪዎች አንዷ እንዲህ ብለዋል፡-

"በአብዛኛዎቹ ጉዳዮች ላይ የታጠቀ ቡድን አመራሮችን በተለይም ሴቶችን ለማስጠንቀቅ መልእክት ይልካል። ብዙ ሴት ሰራተኞች ወዲያውኑ ስራቸውን ያቆማሉ። አንዳንድ ግለሰቦች ወደ ሌላ ቦታ ይዛወራሉ። ለምሳሌ እኔ አሁን በያዝኩት የስራ መደብ የተሾምኩ አምስተኛዋ ሴት ነኝ። ማስፈራሪያው ከቀጠለ በዚህ ቦታ የምቆይ አይመስለኝም።"

**3) የባህላዊ ሚና እንደገና ማቆጥቆጥ እንደ ሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት፡-**

ስጋት እና ቀውስ በሚከሰትበት ወቅት የተዛባ የማህበረሰብ አመለካከት እንደ አዲስ በመስፋፋት የቤት ውስጥ ሃላፊነትን እና ሚናን ያዛባል። በሌላ በኩል የተዛባ አመለካከትና የባሕል ተጽዕኖ የሴቶችን ሚና እንደ እንክብካቤ የማድረግና ለወንዶች የመገዛት በማድረግ ተጽዕኖ ያሳድርባቸዋል። በሌላ በኩል የወንዶቹን ሚና እንደ "ምርጥ አመራር" ወይም "ጠንካራ ወንድ" ጠንካራ የፖለቲካ አመራር ጋር በማመሳሰል ይመድባል ፣ በዋናነት በቀውስ ወቅት የሴቶችን ሚና ችላ ይላል ፣ በዚህም መሰረት በጥናቱ እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 ያሉ ቀውሶች የተለመዱና የተዛቡ ሚናዎችን በማነቃቃት እንደሚቀጥሉ ታውቋል። በችግር ጊዜ ወንዶቹ ቤተሰብን የመጠበቅ ግዴታቸውን የመወጣትና ጠንካራ የወንድነት አመለካከት ሚናን ይጫወታሉ። ሴቶች በተለይ ለአንዳንድ አካላዊ አደጋዎች እንጋለጣለን ወይም ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ይደርሱብናል ብለው ያምናሉ። በሌላ በኩል ወንዶች የጠንካራ ወንድነት አመለካከትን በመያዝ ራሳቸውን ተጠያቂ እንደሆኑ እና ለቤተሰባቸውም ሆነ ለአገራቸው ጠባቂ እንደሆኑ አድርገው ይቆጥራሉ። በዚህም ምክንያት ግጭት በተፈጠረ ቁጥር ወንዶቹ ቤተሰባቸውን ፣ አገራቸውን እና ድንበራቸውን የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው አድርገው ያስባሉ። ከዚህ ጋር ተያይዞ በቁልፍ ምላሽ ሰጪ ቃለ መጠይቁና በትኩረት ቡድን ውይይቱ የተሳተፉ ተሳታፊዎች በኮቪድ-19 የእንቅስቃሴ ገደቦች/ክልከላዎች ወቅት የሴቶች የተለመዱ ሚናዎች መነቃቃትና ተጠናክረው መቀጠላቸውን አረጋግጠዋል። በኮቪድ-19 ወቅት ወንዶች የማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተግባራት ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ሴቶች ደግሞ እንደ ቤተሰብ ተንከባካቢ እና ደህንነት እና ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው የቤት ውስጥ ስራ የሚያከናውኑ ሆነው ታሪካዊ ሚናቸውን ሙሉ በሙሉ ቀጥለው ነበር። በዚህ ምክንያት የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እየቀነሰ በመምጣቱ የቀድሞው የተዛባ የወንዶች እና የሴቶች ሚና እንደገና እያቆጠቆጠና እያገረሸ ሊመጣ ችሏል። በሌላ በኩል ይህ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲቀንስ እና የወንዶች የፖለቲካ የበላይነት እንዲሰፍን አድርጓል።

በጥናቱ መሰረት ወንድ አመራሮች በግጭት እና እንደ ኮቪድ-19 ባሉ ወረርሽኞች የውሳኔ አሰጣጡን ሂደት ይቆጣጠራሉ። ይህንን ሃሳብ ሁለት ምክንያቶች ይደግፋሉ፡- አንደኛ በችግር ጊዜ አብዛኞቹ ወንድ አመራሮች የሴቶችን ጥንካሬ በተለይም ችግርን ማለፍ የሚችሉባቸውን ዘዴዎች መገንዘብ አይችሉም። በሁለተኛ ደረጃ ግጭቱን እንዴት መቆጣጠር እንደሚቻል ወይም የሰላምን ጉዳይ ወደፊት ለማራመድ በሚደረገው ውይይት ላይ ሴቶች በተለያዩ ምክንያቶች መሳተፍ አይፈቀድላቸውም። እነዚህም አጣዳፊነት ፣ መደበኛ ያልሆኑ የግንኙነት መረቦች እና ቸልተኝነት ናቸው።

## 4) **አጣዳፊነት/የጉዳዩ አስቸኳይነት እንደ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት:-**

እንደግጭት እና ኮቪድ-19 ያለ ቀውስ ሲፈጠር ፈጣን እርምጃ መውሰድ የሚያስፈልጋቸው ድንገተኛ ሁኔታዎች ይከሰታሉ። በአስቸኳይ ሁኔታ ምክንያት አመራሮች በዋናነት ወንዶች በካቢኔ ውስጥ ካሉት ሴቶች ባልደረቦቻቸው ሙሉ አስተያየት ሳይቀበሉ ውሳኔዎችን የመወሰን እድላቸው ሰፊ ነው። ይህም ስልጣን ያላቸውን ሴቶች ዕድሎች በማጥበብ ከውሳኔ አሰጣጥ እንዲገለሉ ያደርጋል ፣ (NDI ፣ 2020) አስቸኳይ እርምጃ ለሚፈልጉ ጉዳዮች ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ የፆታ እኩልነትን ግምት ውስጥ ሳያስገባ ስለሚሰጥ የሴቶችን ድምጽ ይቀንሳል። በችግር ጊዜ የሚደረጉ ውሳኔዎች ሁሉ ዲሞክራሲያዊ አይደሉም ፤ ይህም የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ጨምሮ በህዝቡ ህይወት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ የሚገድብ ነው። ከአማራ ክልል ምዕራብ ወሎ ዞን ከመጡ መረጃ ሰጪዎች መካከል አንዷ እንዲህ ብለዋል:-

> "በመደበኛ ሁኔታዎች ወቅት ፆታን ጨምሮ ውሳኔዎች ሲወሰኑ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ይታያሉ። የሀብት ክፍፍልም ይሁን ሌላ ማንኛውም ስልታዊ ውሳኔ የሁሉንም የሚመለከታቸው አካላት ሃሳብ ማስረፅን ይጠይቃሉ። ነገር ግን ግጭቶች እና ኮቪድ-19 ወንዶች ሴቶችን ሳያማክሩ ነገሮችን የሚወስኑበት አዲስ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ አድርገዋል ፣ በመሆኑም በእነዚህ ሁኔታዎች ወቅት ሴቶችን ሳያማክሩ ውሳኔዎች ስለሚወሰኑ የሴቶችን ተሳትፎ ወደ ኋላ ይጎትታሉ/ያስቀራሉ።"

**5) መደበኛ ያልሆኑ የግንኙነት መረቦች እንደ ሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት፡-**

ግጭቶች/ስጋቶች የሴቶችን የዕለት ተዕለት ህይወት ህዝባዊ እንቅስቃሴ መገለል ያባብሳሉ (NDI ፣ 2020)። ከላይ እንደተገለጸው እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 ያሉ ስጋቶች የሴቶችን ደህንነት እና ሰላም አደጋ ላይ ይጥላሉ። በሌላ በኩል ይህ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ እና በሌሎች የህዝብ ህይወት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ይገድባል። ስጋት በሚፈጠርበት ጊዜ ወንድ አመራሮች መደበኛ ያልሆኑ የግንኙነት መረቦችን የመጠቀምና ውሳኔዎችን የመወሰን እድላቸው ሰፊነው። ይህም በሀብት ክፍፍል ላይ ውሳኔዎችን ማድረግ እና የኃላፊነት ቦታ መያዝን ሁሉ ይጨምራል ፣ ይህም ሴቶች በፖለቲካ እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ያላቸውን የውክልና እኩልነት በእጅጉ ይቀንሳል። በወረርሽኙ አጣዳፊነት እና ድንገተኛነት ምክንያትም ዋናው ቡድን ለኮቪድ-19 ምላሽ ለመስጠት ሁሉንም ውሳኔዎች ብቻዉን እንዲያደርግ ይመረጣል። በተጨማሪም ከቁልፍ ምላሽ ሰጪ ቃለ መጠይቁና ከትኩረት ቡድን ውይይቱ በተገኘው መረጃ መሰረት ግጭት እና ኮቪድ-19 በቀውስ አያያዝ ውስጥ ያልተሳተፉ ሴቶችን የሚያገሉ መደበኛ ያልሆኑ አውታረ መረቦች እንዲፈጠሩ ማድረጉ ተረጋግጧል። ይህም በድህረ ግጭት ወቅት የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ጎድቷል።

**6) የሴቶችን ሚና አጉልቶ አለማሳየት እንደ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት፡-**

በቁልፍ ምላሽ ሰጪ ቃለ መጠይቁና በትኩረት ቡድን ውይይቱ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት አመራሮች በዋናነት ወንዶች በሰጡት ምላሽ የሴቶችን ሚና አጉልቶ አለማሳየት የሚመነጨው ከቀውስ በፊት ፣ በቀውስ ጊዜ እና በድኅረ ቀውስ እንዲሁም በኮቪድ-19 ወቅት ሴቶችን በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ማሳተፍ ያለውን ጠቀሜታ ካለመገንዘብ አሊያም በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ቦታ ካለመረዳት የተነሳ እንደሆነ ተናግረዋል። ከተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲ-ኢዜማ አንዷ እንዲህ ብለዋል:-

> “ግጭት በሚከሰትበት ጊዜ ወንዶቹ ሁሉንም ውሳኔዎች ያደርጋሉ። ለምሳሌ በጋሽና ግንባር ከሌሎች ባልደረቦቼ ጋር ተሳትፌያለሁ። ሴት ከሆንሽ ማንም ስለአንቺ አያስብም።

ግጭት በዋነኛነት የሚጎዳው ሴቶችን ቢሆንም ወንዶች ግን ውይይቶችን እና ምርጫዎችን ይቆጣጠራሉ። በከፍተኛ የሃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ ሴቶች እንኳን ከግጭት ጋር በተያያዙ ውሳኔዎች ላይ ምንም ተጽእኖ አላሳዩም ይልቁንም እንደ ምልክት/ማሚያ ብቻ ያገለግላሉ። ከዚህ ባለፈ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሴት መር የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ግጭቶችን በሚፈቱበት መንገዶች ዙሪያ ያላቸው ተጽእኖ በጣም አናሳ ነው። ሴቶች ከግጭቱ በፊትና በግጭቱ ወቅት አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጥቃት እንዲሁም ዛቻ ፣ ይደርስባቸው ነበር። ከግጭት በኋላ ያለው ሁኔታም መሻሻል አልታየበትም ፤ ምክንያቱም ለስነ ልቦናዊ እና አካላዊ ጥቃቶችና ስጋቶች ይጋፈጣሉ።”

በቦረና ዞን የሞያሌ ወረዳ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደተናገሩት ሴቶች በፖለቲካ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ያላቸው ተሳትፎ በተለይ በግጭት ጊዜ ይቀንሳል። ይህ የሆነበት ምክንያት ወንዶች በተለይም በችግር ጊዜ መደበኛ ያልሆኑ አውታረ መረቦች ስላሏቸው ነው። ከቦረና ከመጡ መረጃ ሰጪዎች አንዷ እንደተናገሩት፡-

“የመግባቢያ ቻናል የግል እና የአንድ ወገን ነው። ለደህንነት ሲባል ግን በከፍተኛ አመራሮች ደረጃ ወንዶች ብቻ እርስ በርስ መረጃን በንቃት ይለዋወጣሉ። ከስራው ባህሪና ከሁኔታዎች አስገዳጅነት አንጻር ሴቶች በእነዚህ ተግባራት ውስጥ መሳተፍ አይችሉም። ብዙውን ጊዜ ስብሰባዎች እና ሌሎች እንቅስቃሴዎች በሁሉም ሰአታት የሚከናወኑ ሲሆን ምንም የተወሰነ የጊዜ ሰሌዳ የላቸውም። በዚህ ምክንያት ስርዓቱም ሆነ ሴቶች ራሳቸው ሴቶችን ከእንደዚህ አይነት ተሳትፎ ያገላሉ።”

በተጨማሪም እንደ ኮቪድ-19 ባሉ ወረርሽኞች ወቅት የሴቶችን ሃላፊነት ችላ ማለትን ተከትሎ የወንዶች የበላይነት ታይቷል። በኮቪድ 19ኝ መከሰት ምክንያት ሴቶቹ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ወንዶቹ አጋጣሚውን ተጠቅመው የሴቶቹን ተሳትፎና ተጽእኖ ችላ በማለት ሁሉንም ውሳኔዎች እንደተቆጣጠሩ በጥናቱ ተረጋግጧል።

7) **አድሏዊ የደህንነት** ጥበቃ እንደ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት፡-
ምንም እንኳን ሴቶች በግጭት ምክንያት ለሚፈጠሩ ቀውሶች የበለጠ የተጋለጡ እና ልዩ የደህንነት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ቢሆንም ግጭት በወንዶችም ሆነ በሴቶች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ሴቶች ተጨማሪ ጥበቃ ቢያስፈልጋቸውም ሴትም ሆኑ ወንድ አመራሮች ተመሳሳይ የደህንነት ጥበቃ ማግኘት አለባቸው። በአንጻሩ ግን ጥናቱ በተካሔደባቸው ዞኖች የደህንነት ጥበቃዎች ሲሰጥ የነበረው ለወንዶች ብቻ ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ አሁን ለሁሉም የካቢኔ አባላት የእጅ ሽጉጥ የተፈቀደ ቢሆንም ወንዶች ብቻ ናቸው የሚይዙት። ከአፋር የጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል አንዷ እንደተናገሩት፡-

“በካቢኔ ውስጥ ያሉት ወንዶች በቀውስ/በችግር ጊዜ በተለይም በታጣቂ ቡድኖች እና በመንግስት ሃይሎች መካከል ግጭት በሚፈጠርበት ወቅት ከጠባቂዎቻቸው ጋር ይጓዛሉ አለበለዚያ ቢያንስ እንደሽጉጥ ያሉ የራሳቸው መሳሪያዎች አሏቸው። ይሁን እንጂ ሴት ካቢኔዎች የራሳቸው ሽጉጥም ሆነ የደህንነት ጠባቂ የላቸውም።ስለዚህ ይህ በተለይ በቀውስ/በችግር ጊዜ የመንቀሳቀስ እና የፖለቲካ ተሳትፏችንን ይገድባል።”

## 8) የኢኮኖሚ እጥረት ስጋት እንደ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት፡-

ግጭት እና ኮቪድ-19 አለመረጋጋትን የሚፈጥሩ እና በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ሁለት የተለመዱ ስጋቶች ናቸው። በዋነኛነት ከፖለቲካ ፓርቲዎች የመጡት መረጃ ሰጭዎቹ ኮቪድ-19 እና ግጭት በአባሎቻቸው ኢኮኖሚያዊ አቅም ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደረባቸው ገልጸዋል። በተለይ በራሳቸው የገቢ ምንጭ የሚተዳደሩ ሴት የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች እና አባላት ቀውሱ/ ግጭቱ በኢኮኖሚያቸው ላይ ባስከተለው ተጽዕኖ ድንጋጤ ውስጥ መግባታቸውንና መጎዳታቸውን ገልጸዋል። ከተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አንዱ ከሆነው ከኢዜማ የመጡት እንደተናገሩት:-

"አባሎቻችን በተለይም ለፓርቲያችን በፋይናንሺያል እና በበጎ ፈቃደኝነት ሲሰሩ የነበሩት ከኮቪድ-19 በኋላ ጠፍተዋል። ባለፉት ሁለት አመታት አብዛኛው ጎብኝዎቻችን ወጥተዋል። ተነሳሽነታቸው ፣ ተሳትፏቸው እና አስተዋፅዖአቸው ሁሉም ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል። ምንም እንኳን ኮቪድ-19 በመላው ድርጅታችን ላይ ተጽእኖ ቢያሳድርም በሴቶቹ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ግን ከባድ ነበር።”

## 9) የፖለቲካ ተሳትፎ ፍላጎቶች መቀነስ እንደ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እንቅፋት፡-

ዓለም የተረጋጋች ሳትሆን ስትቀር የሥነ ልቦናዊ ሥጋቶች ይፈጠራሉ ፣ በዚህ ምክንያት ብዙ ሴቶች በፖለቲካ ውስጥ ከመሳተፍ ይልቅ ስለ ሕልውናቸው ያስባሉ። መረጃ ሰጪዎችም እንደ ኮቪድ-19 እና ግጭት ያሉ አስደንጋጭ ሁኔታዎች የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ፍላጎት በእጅጉ እንደሚቀንሱ አረጋግጠዋል።

## 2.7. በኢትዮጵያ በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ሂደቶች የሴቶች ተሳትፎ

በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክርቤት ውሳኔ 1325 መሰረት ሴቶች በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። ሆኖም የተለያዩ መሰናክሎች ያጋጥሟቸዋል። የአባታዊ ስርዓት ፣ ስጋት እና የበላይነት ምክንያት ሴቶች አሁንም በብዙ አጋጣሚዎች ከሰላም ግንባታ ሂደቶች ተሳትፎ የተገለሉ ናቸው (ቦሻ ፣ 2018)። ኮቪድ-19 እና ግጭት ሴቶች በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ በእጅጉ ጎድተዋል (ሳራ ፣ 2020)።

ጥናቱ በተካሔደባቸው አካባቢዎች የተሳተፉ ተሳታፊዎች ሴቶች በሰላም ግንባታ ሂደት ውስጥ የበኩላቸውን ሚና መጫወት እንዳለባቸው አረጋግጠዋል። ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገው የትኩረት ቡድን ውይይት መሰረት በህብረተሰቡ በተለይም በፖለቲካ አመራሮች ላይ ያለው የተዛባ አመለካከትና ግንዛቤ ሴቶች በሰላም ግንባታ ሂደት ያላቸውን ሚና የሚሸረሽር በመሆኑ የራሱን ተጽእኖ እንደሚያሳድር አረጋግጧል። የፖለቲካ አመራሮች በተለያየ ብሔር ውስጥ ያለውን የሴቶች የፖለቲካ አመራርነት ተሳትፎ ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በተለየ መልኩ ላያዩት ይችላሉ። ግጭቶችን ለመፍታት እና ሰላምን ለማስፈን በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሴቶች ተሳትፎ እና ውጤታማነት ከፓርቲያቸው ውጪ እንደ ማህበረሰብ መሪዎች በህብረተሰቡ ዘንድ ባለው አመለካከት ከፍተኛ ተጽዕኖ ይደረግበታል።

ስለዚህ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ያደረጉ ብዙ ሴቶች ቢኖሩም ፣ የፖለቲካ ልሂቃኑ እና መላው ህብረተሰብ ሴቶች ግጭት አፈታትና የሰላም ግንባታ ተግባራትን ጨምሮ የፖለቲካ ኃላፊነቶችን የመሸከም ችሎታቸው ላይ የወረደ ግንዛቤ አላቸው። ሴቶች ከሠላም ግንባታ እና ከግጭት አፈታት ጥረቶች ተገለዋል/ተነጥለዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ጥናቱ በተካሔደባቸው አካባቢዎች የተካሄዱት የትኩረት ቡድን ውይይቶችና ቁልፍ ምላሽ ሰጪ ጥያቄዎች ላይ የተሳተፉ አካላት በሰጡት ምላሽ መሰረት ሴቶች ከግጭት በፊት እና በድህረ ግጭት ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆን ከግጭት በኋላ ከነበሩት የሰላም

ግንባታ እና የመልሶ ማቋቋም ስራዎች የተገለሉ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። በተጨማሪም ሴቶች ሰላምን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት የድጋፍ ሚና እንደሚጫወቱ ገልጸው ኃላፊነታቸው ግን ለአገር ሽማግሌዎችና ለተከራካሪ ወገኖች ምግብ ማዘጋጀት ብቻ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ሴቶች እና ወንዶች ሴቶች ከተከበሩ ሽማግሌዎች ወይም ሰላም አስከባሪዎች አጠገብ ተቀምጠው ለመነጋገርም ሆነ ለመደራደር ምንም ዕድል እንደሌላቸው አድርገው ያስባሉ። ብዙውን ጊዜ ሴቶች ብልሃተኛ ስለሆኑ ለግጭት ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች እንደ መረጃ ምንጭ ሆነው ያገለግላሉ። ከጥናቱ ቁልፍ ጥያቄ ምላሽ ሰጪዎች መካከል አንዱ “በግጭት አፈታት እና ሰላም ግንባታ የሴቶች ተሳትፎ ወሳኝ ነው ብለን እናምናለን። ሴቶች ግን በአካባቢያችን እንደዚህ አይነት እድሎች የላቸውም” ብለዋል ይህን ሃሳብ በአፋር ከሚገኙት የትኩረት ቡድን ውይይት ተሳታፊዎች መካከል አንዱ እንደሚከተለው ደግፈውታል፡-

> “በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ሂደቶች የሴቶች ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛ ነው። ወንዶቹ ሴቶች በፖለቲካ ውስጥ እንዲሳተፉ አያበረታቱም ፣ ግጭት አፈታት ላይ በሚካሔዱ እንቅስቃሴዎች ውስጥም አይሳተፉም ፣ ሴቶች እንደ መሪ ፣ ሰላም ፈጣሪ እና አርአያነት በአገር ውስጥ ስለሚኖራቸው ተቀባይነት የተሳሳተ ግንዛቤ አለ። ሴቶች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ አለመግባባቶችን ሲፈቱ እንኳን ወንዶች በምርጫቸው ፈጽሞ አይስማሙም። ህብረተሰቡ በፖለቲካ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እና የዓለምን ሰላም ማስፈን የወንዶች ብቸኛ ኃላፊነት እንደሆነ አድርጎ ይመለከተዋል።”

## 2.8. የንፅፅር ግምገማ በክልል ከተሞች

ከላይ በመግቢያው እንደተገለፀው ጥናቱ በሶስት ክልላዊ መንግስታት ማለትም በአፋር ፣ በአማራ እና በኦሮሚያ ክልል የተወሰነ ነው። የቁልፍ ምላሽ ሰጪ ጥያቄዎችና የትኩረት ቡድን ውይይት ውጤቶች እንደሚያሳዩት ኮቪድ-19 በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው። ሴቶቹ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የተገለሉበት እንደ ተቋማዊ ፣ የቤት ውስጥ እና የግል ደህንነት ምክንያቶች ተመሳሳይ ናቸው። በሌላ በኩል ግጭቶች በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ እንደ ነባራዊ ሁኔታው ከክልል ክልል እንደሚለያይ ለማወቅ ተችሏል። ለምሳሌ በአማራ እና አፋር ክልሎች የግጭቱ ዓይነት የተለመደ ነበር ፣

ግጭቱ በታጣቂ አካላት መካከል ሲሆን በአካባቢው የተለመደው ግጭት መጠናከር የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ተጽዕኖ ፈጥሯል። በኦሮሚያ አልፎ አልፎ በአማፂያን የሚፈጸሙ ጥቃቶች የነበሩ ሲሆን ግጭቶቹ እና ሽኩቻዎች በዋናነት በአካባቢው ገዥዎች እና በአማፂ ቡድኖች መካከል ነበሩ።

# ምዕራፍ ሶስት

## ማጠቃለያ እና ምክረ ሃሳቦች

### 3.1. ማጠቃለያ

እንደ ኮቪድ-19 ፣ ግጭት እና አስቸኳይ ጊዜ ውሳኔዎችና ምላሽ አሰጣጦች ያሉ ቀውሶችና ስጋቶች ከስርዓተ-ፆታ አድሎ ገለልተኛ አልነበሩም። ሴቶቹን ፆታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች ፣ ብዝበዛ ፣ በደል ፣ የጾታ እና የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ተደራሽነት መቀነስ ፣ የጤና አገልግሎት እንደ ቅድመ ወሊድ ፈተናዎች ፣ ስነ-ልቦናዊ ጥቃቶችና ለተጨማሪ ችግሮች አጋልጠዋል። ቀውሱን ለመፍታት በፓርላማ በተቋቋሙ የውሳኔ ሰጪ እና ግብረ-ሀይል ኮሚቴዎች ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎና አመራርነት ማረጋገጥ ወሳኝ ነው።

ወረርሽኞች ፣ ግጭቶች ፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በሴቶች ማህበራዊ ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የሚያደርሱትን ተፅእኖ ለመለካት ከመደበኛው አሰራር በተጨማሪ ግጭት እና ወረርሽኞች ሴቶች ትርጉም ያለው የፖለቲካ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው እንዴት እንደሚያግዷቸው ተጨማሪ ጥናት ማድረግ ያስፈልጋል። የጥናቱ ዋና ዓላማም ስጋት/ቀውስ በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያስከትለውን ተፅእኖ በኳሊቴቲቭ/ጥራትን መሰረት ባደረገና የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋምን የአሰራር ማዕቀፍ በተከተለ መልኩ (2020) በስጋት ፣ ዲሞክራሲ እና ጾታ መካከል ያለውን መስተጋብር እንዲሁም ግጭቶች እና ኮቪድ-19ኝን የመሳሰሉ ቀውሶች የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ እንዴት እንደሚጎዱ ለመለየትና ለመገምገም ነበር። በዚህም መሰረት ቀውስ ፣ ግጭት እና ኮቪድ-19 የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ እንደሚጎዱ ተረጋግጧል።

በአንደኛ ደረጃ የቀውስ ጊዜ በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ **የደህንነት ስጋት** ተጽእኖ እንደሚያሳድር ተረጋግጧል። ይህም ተቋማዊ ፣ የቤት ውስጥ እና የግል ደህንነትን ያካትታል። ሴቶች በቀውስ ጊዜ በሚሰሩበት ተቋም ፣ በግል ህይወታቸው ወይም በራሳቸው ላይ የሚደርሱ የደህነነት ስጋቶች በፖለቲካ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ይገድባሉ። ከዚህ በመነሳት በኦሮሚያ ፣ አፋር እና

አማራ ክልሎች በቁልፍ ምላሽ ሰጪ እና በትኩረት ቡድን ውይይት በተካሄዱት ጥናቶች የተሳተፉ ምላሽ ሰጪዎች በክልል ፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ የተዋቀሩ ተቋማት እና ማህበራት ባለስልጣናት “ግጭት የሚያስከትለውን የቀውስ መጠን ለመረዳትና ለማርገብ/ለማረጋጋት ሃላፊነት አለባቸው” ብለዋል። ወንዶች እነዚህን ተቋማት አስቀድመው ስለሚቆጣጠሩ ፣ ደህንነትን የሚገልጹት ከራሳቸው እይታ/ግንዛቤ አንጻር ነው። በዚህም ክንያት እነዚህ አመራሮች በአብዛኛው ወንዶች ሆነው ሁኔታውን ለመምራት እና ሴቶቹ ቤተሰቦቻቸውን እንዲንከባከቡ ወይም በቁሳቁስና በሰብአዊነት መስክ በመሰማራት ተጨማሪ ሚናዎችን እንዲሸፍኑ በማሳመን ውሳኔ ሰጪዎች ሳይሆኑ እንዲቀሩ ያደርጓቸዋል።

በሁለተኛ ደረጃ በቀውስ ወቅት በዋናነት በግጭት ጊዜ በተለያዩ አካላት የሚደረግ **ማስፈራራት** የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ከሚገድቡ ዋና ዋና እንቅፋቶች አንዱ ነው። በተለይ በኦሮሚያ ፣ በአማራና በአፋር ክልሎች የታጠቁ ኃይሎች በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች የሴት ፖለቲከኞች (የፖለቲካ ፓርቲ እጩዎችም ሆኑ የመንግሥት ካቢኔዎች) በፖለቲካው መስክ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ በጥናቱ ተረጋግጧል። ምክንያቱም የታጠቁት ቡድኖች ፖለቲከኞች በዋነኛነት ሴቶች በዞንና በወረዳ ከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃ ላይ እንዳይወጡ ለማድረግ ስነ ልቦናዊ እና አካላዊ ማስፈራራትን ይፈጽማሉ። ሴቶችን ለማስጠንቀቅ እና ጭንቀትን ለመፍጠር የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። እነዚህ ማስፈራሪያዎች ሰዎች መኖሪያቸውን እንዲቀይሩ እና ስልጣናቸውን እንዲለቁ ያደርጓቸዋል።

በሦስተኛ ደረጃ ፣ **ከባህላዊ ሚና** ጋር በተያያዘ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚጎዳ ሌላ ምክንያትም ተገኝቷል። ይህ አመለካከት ወንዶቹን እንደ “ምርጥ መሪዎች” ወይም “ጠንካራ ሰው” አድርጎ መውሰድ ሲሆን ከፖለቲካ አመራርነት አንጻርም ተመሳሳይ ሲሆን በቀውስ ወቅት በዋናነት የሴቶች ሚና ችላ ይባላል። በዚህም መሰረት በጥናት ግኝቱ እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 ያሉ ቀውሶች የተለመዱ ባህላዊ ሚናዎችን ማነቃቃት እንደሚቀጥሉ ታውቋል። በቀውስ ጊዜ ወንዶች ቤተሰብን የመጠበቅ ግዴታቸውን በመወጣት ጠንካራ የወንድነት አመለካከትን ይይዛሉ።

ሴቶች በተለይ ለአንዳንድ አካላዊ አደጋዎች ለምሳሌ ፆታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች እንደሚጋለጡ ያምናሉ። በተጨማሪም ወንዶቹ ራሳቸውን ተጠያቂ እንደሆኑ እና ለቤተሰባቸውም ሆነ ለአገራቸው ጠባቂ እንደሆኑ አድርገው ይቆጥራሉ። በዚህም ምክንያት ግጭት በተፈጠረ ቁጥር ወንዶቹ ቤተሰባቸውን፣ አገራቸውን እና ድንበራቸውን የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው አድርገው ይቆጥራሉ።

በአራተኛ ደረጃ **አጣዳፊ/አስቸኳይ ውሳኔ** የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ወደ ኋላ ለመጎተት አስተዋፅኦ ያደርጋል። በአብዛኛው እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 ያሉ ስጋቶች ፈጣን ምላሽ/እርምጃ የሚያስፈልጋቸው ድንገተኛ ውሳኔዎችን ይፈልጋሉ። በአጣዳፊ/በችኮላ ውሳኔ ምክንያት መሪዎች (በዋናነት ወንዶች) በካቢኔ አባላት ውስጥ ካሉት ሴት ባልደረቦቻቸው ሙሉ አስተያየት ሳይጠይቁ ውሳኔዎችን የመወሰን እድላቸው ሰፊ ነው። በዚህ ጊዜ የሚደረጉ ውሳኔዎች ሁሉ ዲሞክራሲያዊ አይደሉም። ይህም የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ጨምሮ በህዝብ ህይወት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ የሚገድብ ነው።

በአምስተኛ ደረጃ በቀውስ ጊዜ የሚፈጠረው **መደበኛ ያልሆነ የግንኙነት** መረብ/ኔትወርክ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ይጎዳል። እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 ያሉ ስጋቶች የሴቶችን ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላሉ። በሌላ በኩል ይህ ሴቶች የፖለቲካ እና የሌሎች የህዝብ ህይወት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ይገድባል። ስጋት በሚፈጠርበት ጊዜ ወንድ መሪዎች መደበኛ ያልሆኑ የግንኙነት መረቦችን እና ውሳኔዎችን የማድረግ እድላቸው ሰፊ ነው። ይህም በሀብት ላይ ውሳኔዎችን ማድረግ እና የኃላፊነት ቦታዎችን ያካትታል፡፡ ሁለቱም ሴቶች በውሳኔ አሰጣጥ እና በፖለቲካ ተሳትፎ ውስጥ ያላቸውን የውክልና እኩልነት በእጅጉ ይቀንሳሉ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ወረርሽኝ አስቸኳይነትና ድንገተኛ ሁኔታ ምክንያት ለኮቪድ-19 ምላሽ ለመስጠት ተጽእኖ ፈጣሪው ቡድን ሁሉንም ውሳኔዎች ብቻውን ለማድረግ ይገደዳል።

በስድስተኛ ደረጃ **ሴቶች በፖለቲካ ተሳትፎ ያላቸውን ሚና ችላ ማለት** የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ይጎዳል። ከቁልፍ ምላሽ ሰጪ እና ከትኩረት ቡድን ውይይት ጥያቄዎች በተሰበሰበው መረጃ መሰረት ሴቶች ለእንደዚህ አይነት

ግጭት እና ኮቪድ-19 በቅድመ ስጋት እና ድኅረ ስጋት ጊዜ የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ ችላ የማለት ከፍተኛ አዝማሚያዎች ተስተውለዋል። በትኩረት ውይይት ቡድኑ ላይ የተሳተፉት መሪዎች (በዋናነት ወንዶች) ሴቶችን በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ማሳተፍ ያለውን ጠቀሜታ አለመገንዘባቸውን እንዲሁም በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ቦታ እንደማይረዱ ተናግረዋል።

በሰባተኛ ደረጃ **የደህነት ጥበቃና ከለላ ሚና** መደባለቅ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚጎዳ ነው። ምንም እንኳን ሴቶች ተጨማሪ ጥበቃ ቢያስፈልጋቸውም ሴትም ሆኑ ወንድ መሪዎች ተመሳሳይ የደህንነት ጥበቃ ማግኘት አለባቸው። በአንጻሩ የደህንነት ጥበቃ ኃላፊነቶች ጥናቱ በተካሔደባቸው አካባቢዎች ላይ ለወንዶች ብቻ ይሰጣሉ። በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ ለሁሉም የካቢኔ አባላት የእጅ ሽጉጥ ተፈቅዶላቸዋል ሆኖም ግን ወንዶች ብቻ ናቸው የሚጠቀሙበት።

በመጨረሻም **የኢኮኖሚ እጥረት ስጋት እና የሴቶች ዘንድ የፖለቲካ ተሳትፎ ፍላጎቶች መቀነስ** ለሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ መጎልበት የጎንዮሽ ጉዳትን ያስከትላል። በአንድ በኩል ግጭት እና ኮቪድ-19 መረጋጋትን የሚፈጥሩ እና በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ሁለት የተለመዱ ስጋቶች ናቸው። በዋነኛነት ከፖለቲካ ፓርቲዎች የመጡት የጥናቱ ተሳታፊዎች (መረጃ ሰጭዎች) ኮቪድ-19 እና ግጭት በአባሎቻቸው ኢኮኖሚያዊ አቅም ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደሩባቸው ገልጸዋል። በሌላ በኩል ለሰላም ግንባታ ሂደት ሴቶች የበኩላቸውን ሚና መጫወት እንዳለባቸው ለማወቅም ተችሏል። ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉት ውይይቶች በህብረተሰቡ በተለይም በፖለቲካ አመራሮች ላይ ያለው አመለካከትና አረዳድ የሴቶችን ሚና በመቀነሱ በሰላም ግንባታው ዘርፍ እንዳይሰማሩ የራሱን አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት አረጋግጠዋል። የፖለቲካ አመራሮች በአንድ የተወሰነ ብሔር ውስጥ ያሉ ሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በተለየ መልኩ ላያዩት ይችላሉ። ማህበረሰቡ በሴቶች ላይ ያለው የተዛባ አመለካከት ሴቶች ግጭቶችን ለመፍታት እና ሰላምን ለማስፈን በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ገለልተኛ አመራር በመሆን የሚኖራቸውን ተሳትፎ እና ውጤታማነት ማሳደግ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል።

## 3.2. ምክረሃሳቦች

በጥናቱ ግኝቶች መሰረት በዘርፉ ለሚሰሩ ባለድርሻ አካላት የሚከተሉት ምክረ ሃሳቦች ተሰንዝረዋል፡-

- **የአቅም ግንባታ፡-** ·መጪውን ጊዜ ለመለወጥ የሴት ህግ አውጪዎችን እና በተለያዩ ዘርፎች ያሉ ባለሙያዎችን አቅም ማሳደግ ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ስለሆነም የገንዘብ አቅም ግንባታ ውጥኖች የሴቶችን ብቃት በተለይም በፖለቲካ ውስጥ ፣ ገላጭ እና ተጨባጭ በሆነ ደረጃ ያሻሽላል። ከሥርዓተ-ፆታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ለምሳሌ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ፣ እንደ የአቅም ግንባታ ውጥኖች ውጤታማ የሚሆኑት ቁርጠኛ ሥርዓተ-ፆታ ተሳትፎ ሲኖር ነው። ይህም ቁርጠኝነት ዝግጁነትን ለማጠናከርና ችግሮችን የመቋቋም ችሎታን ለመፍጠር ይረዳል።
- **ጥናትና ምርምር ማድረግ፡-** እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 ባሉ ቀውሶች ውስጥ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ ፣ ፖሊሲዎችን ለመደገፍ እና ተፅእኖ ለማድረግ እውነተኛ እና ተጨባጭ መረጃዎች ያስፈልጋሉ። በመሆኑም በዘርፉ ጥናትና ምርምርን ማስፋፋት ሰላምን ለመፍጠር እና ሰፊ የፖለቲካ ተሳትፎ ለማድረግ ተነሳሽነትን ይፈጥራል።
- **ለሴቶች ደህንነት እና ሠላም ትኩረት መስጠት፡-** በቂ የሆነ የደህንነት ጥበቃ በማይኖርበት ጊዜ በተለይም በሁከት እና ባለመረጋጋት ጊዜ ሴቶች በፖለቲካ ውስጥ የመሳተፍ እድላቸው አነስተኛ ነው። ሴቶች ለደህንነታቸው እና ለሰላማቸው ከፍተኛ ዋጋ ስለሚሰጡ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ ጠንካራ የደህንነት ጥበቃ ስርዓት መዘርጋት የግድ ነው።
- **ቀውስን መሰረት ያደረገ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት/ሜይንስትሪሚንግ ፕሮግራም፡-** እንደ ግጭት እና ኮቪድ-19 ለመሳሰሉት ቀውሶች ምላሽ ለመስጠት ልዩ የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ፕሮግራም ያስፈልጋል። እንደ ፖለቲካ ባሉ ቀውሶች የሚመሩ የሥርዓተ-ፆታ ኢ-ፍትሃዊነት መጠን የሥርዓተ-ፆታ ማካተት ፕሮግራሞችን በመተግበር ይቀንሳል።

- **የሴቶችን ትስስርና የሴት አደረጃጀት ተቋማትን ማጠናከር፡-** በሴቶች በተመሰረቱ ቡድኖች መካከል ጥብቅ የግንኙነት ሰንሰለት መፍጠር የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ከማበረታታት ባለፈ ጥልቅ እና ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ችግሮች ማስወገጃ ዘዴዎችን በማጎልበት ፣ የሴቶችን ውክልና በማጎልበት እና በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ሂደቶች ላይ ተጽእኖ የማድረግ ችሎታን ይዳብራል። ሴቶች አንድ የጋራ አጀንዳ እንዲያወጡ እና ለችግሮቻቸው መፍትሄ እንዲፈልጉ የሚያግዙ የግንኙነት መረቦችን ፣ መድረኮችን እና ስብሰባዎችን ማበረታታት ወሳኝ ነው። የሴቶች እና ሴቶችን መሰረት ያደረጉ ቡድኖችን በአገር ውስጥ ፣ በአገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስፋፋት ሴቶች ግጭቶችን በመፍታት ፣ ሰላምን በማስፈን እና በፖለቲካ ውስጥ በመሳተፍ ያላቸውን ፋይዳ ያጠናክራል።
- **አካታች የሆነ የቀውስ አስተዳደር/አያያዝ፡-** ይህንን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል ከሚያሳዩት ጥቂት ምሳሌዎች መካከል ብዙ ሴቶችን በአመራርነትና በውሳኔ ሰጪነት ደረጃ በማሳተፍ ፣ ከሴቶች መብት ተሟጋች ድርጅቶችና አመራሮች ጋር በሰላማዊ ድርድር ላይ ምክክር መደረግ እንዳለበት በማያሻማ ሁኔታ በመግለጽ ፣ ሴቶች በከፍተኛ ደረጃ በሰላም ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ በማበረታታት ፣ በተለያዩ ደረጃዎች ሴቶችን በማካተት የወንዶችን ቴክኒካል እውቀት ማሻሻል እና የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችንና የሰላም ግንባታ ሂደቶችን በሁሉም ደረጃዎች ውስጥ ማካተት ናቸው።
- **የማህበረሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፡-** የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ የችግሩን የወደፊት ክስተቶች ከመቀነሱም በላይ የአሁኑን ችግር ያጠፋል። ስለዚህ ማህበረሰቡን ማነቃቃት የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የማሳደግ ትልቁን ግብ ቀላል ያደርገዋል። በአካባቢ ፣ በክልል እና በአገር አቀፍ ደረጃ የምሥክርነት እና የችሎት ጥያቄዎች ፣ የመንግስት አካላትን ቴክኒካል ድጋፍ እና ግብረ መልስ ማዘጋጀት ታላቅ እገዛ ያደርጋል።

- **የኮታ ሥርዓትን መዘርጋት፡-** የወንዶችና የሴቶች ጥምረት ላይ መሰረት ያደረገ ፖሊሲ ፣ ህግ እና ደንቦች አለመኖራቸው በመደበኛ እና በአስቸኳይ ሁኔታዎች ውስጥ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማረጋገጥ እንቅፋት ይፈጥራል። በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች ውስጥ ያሉ ግጭቶች እና እንደ ኮቪድ-19 ያሉ የጤና ቀውሶች በፆታ የተለየ መረጃ አለመኖር ጉዳቱን መቀነስ ፣ ምክንያታዊ ውሳኔዎችን እና ውጤታማ መፍትሄዎችን እንዴት እንደሚያደናቅፍ ምሳሌዎች ሆነው ያገለግላሉ። የሴቶችን የመሪነት ሚና እና የውሳኔ ሰጭነት ሀላፊነቶች ተደራሽነት ለማሳደግ ኮታ እና የመጠባበቂያ ፖሊሲዎችን በቋሚነት መደገፍ ለሴቶች ተሳትፎ አስፈላጊነው። የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማሳደግ በስራ ቦታዎችና በህብረተሰቡ ውስጥ የስርዓተ-ፆታ ኮታንና ህጎችን መተግበር አስፈላጊ ነው።
- **የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ አካባቢያዊ ማድረግ፡-** ጥናቱ እንደሚያሳየው ምንም እንኳን በፌዴራል ደረጃ የሥርዓተፆታ ኢ-ፍትሃዊነትን የመቀነስ ውጥኖች ቢኖሩም የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እስካሁን በአካባቢ ደረጃ አልተካተተም። መደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑ ተቋማትም ይህንን አሳይተዋል። በፖለቲካ መድረኮች በተለይ እንደ ኮቪድ-19 እና ግጭት ባሉ ቀውሶች ውስጥ ያሉ አካባቢዎች ላይ የሥርዓተ-ፆታ ልዩነትን የሚቀንሱ አሰራሮችን መዘርጋት አስፈላጊ ነው።

# ዋቢ መጽሐፍት

Agbajobi, D., (2010). 'The Role of Women in Conflict Resolution and Peacebuilding', in eds. R. Bowd and A. B. Chikwanha, understanding Africa's Contemporary Conflicts, African Human SecurityInitiative, pp. 233-254

Anderlini, S. Naraghi. (2007). Women Building Peace: What They Do, Why It Matters. London: Lynne Rienner.

Ashild Falch. (May, 2010). Women's Political Participation and Influence in Post-Conflict Burundi and Nepal. Peace Research Institute Oslo (PRIO) research paper.

Bosha, Sarah L., (2018). The Importance of Gender Equality and Women's Inclusion for Resolving Conflict and Sustaining Peace', in William Durch, Joris Larik, and Richard Ponzio (eds)Just Security in an Undergoverned World (Oxford, 2018; online edn, Oxford Academic, accessed 25 Sept.2022.https://doi.org/10.1093/oso/9780198805373.003.0005,

Campbell, Patricia J., (2005).'Gender and Post-Conflict Civil Society: Eritrea,' International Feminist Journal of Politics 7(3):377-99

Cardona, I. et al. (2012), From the Ground Up: Women's Role's in Local Peace Building in Afghanistan, Liberia, Nepal, Pakistan and Sierra Leone, Action Aid, Institute for Development Studies and Womankind, London.

CARE International. (March, 2020). Gender Implications of Covid-19 Outbreaks in Development and Humanitarian Settings.

Castillejo, C. (2011), Building a State that Works for Women: Integrating Gender into Post- Conflict State building, Fundación para las Relaciones Internacionales y el Diálogo Exterior (FRIDE), Madrid.

CEPPS. (2020). CEPPS Gender Assessment Report: Ethiopia.April 15, 2020

Cohn, Carol. (2012). Women and Wars: Towards a Conceptual Framework. In Cohn, Carol Cohn (ed.) Women & Wars. Cambridge: Polity Press, pp. 22

Cordaid (2012), Integrating Gender into the New Deal for Engagement in Fragile States, Cordaid, The Hague.

Dibu, W., & Ahadu, E. (2020). Post2018 political reforms in Ethiopia: Its achievements and challenges. Agathos, 11(1), 439-451.

Domingo, P. and R. Holmes (2013), Gender Equality in Peacebuilding and Statebuilding, Overseas Development Institute, London.

Ethiopian Women Lawyers Association (EWLA). (2021). Final Report on Violence against Women in Elections (VAW- E) Observation during the Sixth Ethiopian National and Regional Elections

Federal Democratic Republic of Ethiopian Constitution. (1995). Federal Negarit Gazeta, Addis Ababa.

Fekadu Beyene. (n.d).Assessment on the Role of Women in Peace and Reconciliation in Oromia and Somali Regional States.

Georgetown Institute (2015), Women Leading Peace: Women's Political Participation in Peace Processes in Northern Ireland, Guatemala, Kenya, and the Philippines, Georgetown Institute for Women, Peace and Security, Washington, D.C.

Helena Gronberg. (2020). COVID-19 and its impact on women's participation in peace processes: Challenges and opportunities

IDPS (2016), “Stockholm Declaration: Addressing Fragility and Building Peace in a Changing World”, International Dialogue on Peacebuilding and State building, www.pbsbdialogue.org/media/filer_public/1e/23/1e237c73-5518-4a03-9a87- b1aa6d914d20/stockholm_declaration.pdf.

Inter-Parliamentary Union. (2022). Gender and COVID-19: A Guidance Note for Parliament

International IDEA, (2021). Women’s Political Participation ~ Africa Barometer 2021.

International Republican Institute (IRI) and National Democratic Institute (NDI). (2021). Ethiopia June 21, 2021 National Elections Report.

IPU and UN Women. (April, 2021). Strategic Inter-parliamentary Dialogue Gender-responsive recovery post COVID-19-Hosted by the IPU and organized jointly with UN Women. A series of online meetings from 7 to 21 April 2021: Draft Concept Note

Julia Smith. (2020). “Overcoming The ‘Tyranny Of The Urgent’: Integrating Gender Into Disease Outbreak Preparedness And Response,” Gender & Development 27, no. 2, accessed August 22, 2022, https://doi.org/10.1080 /13552074.2019.1615288

Kassa Shimelis. (2015). Challenges and Opportunities of Women Political Participation in Ethiopia. J Glob Econ 3: 162. doi:10.4172/2375- 4389.1000162

Large, Judith. (1997).‘Disintegration Conflicts and the Restructuring of Masculinity,’ Gender and Development 5(2):23-3.

Lawyers Association (EWLA). (2021). Preliminary Statement on Violence against Women in Elections (VAW-E) Monitoring of the Harari and Somali Regions Elections.

Mathad, Jyothi et al. (2019). Female global health leadership: data-driven approaches to close the gender gap. The Lancet 393(10171). DOI: https://doi.org/10.1016/S0140- 6736(19)30203-X

Menham, Claire et al. (2020). COVID-19: the gendered impacts of the outbreak. The Lancet. DOI https://doi.org/10.1016/S0140-6736(20)30526-2

Myrttinen, H., J. Naujoks and J. El-Bushra (2014), Rethinking Gender in Peacebuilding, International Alert, London.

OECD (2013), Gender and Statebuilding in Fragile and Conflict-Affected Contexts, OECD Publishing, Paris, http://dx.doi.org/10.1787/9789264202061-en.

OECD. (2018). Gender Equality and Women's Empowerment in Fragile and Conflict-affected Situations: A Review of Donor Support. OECD Development Policy Papers.

OECD Publishing, Paris, httpOctober 2017, No. 8.
Paffenholz, T. et al. (2016). Making Women Count – Not Just Counting Women: Assessing Women's Inclusion and Influence on Peace Negotiations, Inclusive Peace & Transition Initiative, Geneva, and UN Women, New York

Peace Research Institute Oslo (PRIO). (2010). Women's Political Participation and Influence in Post-Conflict Burundi and Nepal. PRIO Paper, May 2010

Punam Yadav. (2021). Can women benefit from war? Women's agency in conflict and post- conflict societies. Journal of Peace Research, Vol. 58(3) 449–461. DOI: 10.1177/0022343320905619

Sara E. Davies & Belinda Bennett. ( 2016). "A Gendered Human Rights Analysis Of Ebola And Zika: Locating Gender In Global Health Emergencies," International Affairs 92, no. 5, accessed August 26, 2020, https://doi.org/10.1111/1468-2346.12704.

Sharon Begley. (March 3, 2020). “Who Is Getting Sick, And How Sick? A Breakdown of Coronavirus Risk By Demographic Factors,” https://www.statnews.com/2020/03/03/who-is-getting-sick-and-how-sick-a- breakdown-of-coronavirus-risk-bydemographic-factors/.

Sonya Rupare. (2019). Why Action Aid promote women’s leadership in emergencies? https://actionaid.org/opinions/2019/why-actionaid-promotes-womens-leadership- emergencies

Stephen Mcglinchey, Rosie Walters & Christian Scheinpflug (ed.) (2017). International Relation.Theory.http://www.e-ir.info/wp-content/uploads/2017/11/International Relations-Theory-E-IR.pdf
Tajali, M. (2013). “Gender Quota Adoption in Post-Conflict Contexts: An Analysis of Actors and Factors Involved.” Journal of Women, Politics & Policy 34 (3): 268-269. doi:10.1080/1554477X.2013.820115.

The Inter-American Commission of Women (CIM). (2020). COVID-19 in women’s lives: Reasons to recognize the differential impacts / Comisión Interamericana de Mujeres.p.25 ; ISBN 978-0-8270-7047-9
UN Office for the Coordination of Humanitarian Affairs (OCHA). (2020). “Global Humanitarian Overview 2020,” OCHA, December 4, 2020, https://www.unocha.org/sites/unocha/files/GHO-2020_v9.1.pdf.

UN Women (2010), Women’s Participation in Peace Negotiations: Connections between Presence and Influence, UN Women, New York.

UN Women (2012), UN Women Source Book on Women, Peace and Security, UN Women, New York.

UN Women (2015), Preventing Conflict, Transforming Justice, Securing the Peace: A Global Study on the Implementation of UNSCR 1325, UN Women, New York.

UN Women (2020). Women's Political Participation & Leadership in COVID-19 Response.

UNSG (2010), "Report of the Secretary-General on Women's Participation in ", A/65/354–S/2010/466, Secretary-General of the United Nations, NewPeacebuilding York, www.un.org/en/peacebuilding/pbso/pdf/seven_point_action_plan.pdf.

Wright, H. (2014), Masculinities, Conflict and Peacebuilding: Perspectives on Men through a Gender Lens, Safer world, London.

Wubante Ayalew. (2021). Women and Ethiopian politics: Political leaders' attitude and views on women's effectiveness, Cogent Social Sciences, 7:1, 1948653, DOI: 10.1080/23311886.2021.

# አባሪ

## የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ

### የትኩረት ቡድን ውይይት መመሪያ-ከተለያዩ ዘርፎች ለተውጣጡ ሴቶች

የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ ኮቪድ-19 እና ግጭት በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያስከትሉትን ተፅእኖ ለመገምገም ሃላፊነት የተሰጠው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር (EWLA) ብሔራዊ አማካሪ ድርጅት ነው። በመሆኑም ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነተኛ መልስ ለመስጠት የሚያደርጉልን ትብብር ለዚህ ግምገማ ስኬታማነት በጣም አስፈላጊ ነው። ምላሾችዎ ሚስጥርንነታቸው ተጠብቆ ይያዛሉ። ይህም ለኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ተሳትፎ ብቻ የሚውል መሆኑን እያሳወቅን ለትብብርዎ በቅድሚያ እናመሰግናለን!

1. የኢትዮጵያን የፖለቲካ ምህዳር ከሴቶች አንፃር እንዴት ያዩታል? ሴቶች ወደ ፖለቲካ መድረክ እንዲገቡ የሚያበረታታው እንዴት ነው?
2. የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲወዳደር እንዴት ያዩታል?
3. የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ከወንዶች ጋር ሲወዳደር ለሴቶች በቂ እድል ይሰጣል ብለው ያስባሉ? ካላሰቡ ለምን?
4. በኢትዮጵያ የእርስዎን/የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደናቅፉ ነገሮች ምንድን ናቸው? በዋናነት በችግር ጊዜ?
5. ከሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እና የግጭት አፈታት አንፃር ህብረተሰቡ ስላለው አመለካከት ምን ያስባሉ?
6. ግጭቶች በአካባቢዎ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያደርሱትን ተጽእኖ እንዴት ይገልጹታል? በአከባቢዎ በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የግጭት ተፅእኖን እንዴት ይገልፃሉ፡-
    - ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንደ አካላዊ ጥቃት ፣ ማስፈራራት ፣ጾታዊ ትንኮሳ እና ሌሎች ጾታዊ ጥቃት ከኮቪድ-19 ወዲህ ጨምረዋል?
    - ደህንነት/አለመተማመን ፣ በዋነኛነት ለሴቶች ፣ በቅድመ ግጭት ጊዜ እና በድህረ ግጭት በአካባቢያችሁ እነዴት ነው? የመንቀሳቀስ ደህንነትስ? የህዝብ ንቅናቄ ደህንነትስ? በግጭት ጊዜ ለአደጋ ተጋልጠዋል? እንዴት እና በምን አይነት አደጋ ተጋላጭ ነበሩ? የጥቃት ተጋላጭነት? በነጻነት ለመንቀሳቀስ እና ሀላፊነትዎን ለመወጣት ዋስትና አግኝተዋል?
    - በግጭት ወቅት በዋናነት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ? በግጭት ውስጥ ተሳትፈዋል? እንዴት ተሳትፋችኋል?

- በግጭት ወቅት የምክክር ደረጃ? በግጭት ወቅት የእርስዎ እና የእርስዎ ባልደረቦች በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ያደረጉት ተሳትፎ እንዴት ነበር? በግጭት ወቅት የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቱ አሳታፊ ነበር? በግጭት ወቅት ሴቶችን በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ማግለል የነበረ ይመስልዎታል ፣ በዋነኛነት በአጣዳፊ/በአስቸኳይ ሁኔታ?
- በግጭት ምክንያት የቤተሰብ ኃላፊነት ሸክም ሆኖብዎታል? በችግር/ቀውስ አያያዝ ውስጥ ተሳትፈዋል? በግጭት ወቅት በቤተሰብ እና በቢሮዎ ውስጥ የእርስዎ ሚናዎች ምን ነበሩ?
- በግጭት ወቅት በእርስዎ የአመራር ቦታ ላይ የግንኙነት/ተግባቦት ሁኔታ እንዴት ነበር? በቋንቋ ረገድ ግንኙነቱ ግልጽ ነበር? የመገናኛ ብዙሃን ለሴቶች ምቹ ነበሩ? መረጃ ተደራሽ ፣ ወቅታዊ ፣ ትክክለኛ ነበር?

7. እንደ የካቢኔ ድርሻ ፣ የክልል ምክር ቤት ድርሻ ፣ የአስተዳደር ምክር ቤት ወይም የዘርፍ ውክልና ድርሻ የሴቶች የአመራር ቦታዎች ላይ የግጭት ተጽእኖ እንዴት ያዩታል? ሴቶች በአመራር ቦታዎች ያላቸውን ድርሻ ከግጭት በፊት ከነበረው ሁኔታ ጋር እንዴት ያወዳድራሉ?
8. ኮቪድ-19 በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ያለውን ተጽእኖ እንዴት ያዩታል? (በተለይ 6ኛውን ሀገር አቀፍ ምርጫ ማካሄድ)? ኮቪድ-19 በፖለቲካ ውስጥ የመሳተፍ ችሎታዎን እንዴት ቀነሰው? (በተለይ 6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ)? በፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለመሳተፍ ደህንነትዎን ፣ እንቅስቃሴዎን እና ነጻነትዎን ገድቦ ነበር?
9. በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ተግባራት የሴቶችን ተሳትፎ እንዴት ያዩታል? በእርስዎ አካባቢ ሴቶች በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ እንዴት ይሳተፋሉ? በሰላም ግንባታ ተግባራትስ እንዴት ይሳተፋሉ?
10. ሴቶች በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ተግባራት ፣ በፖሊሲ ፣ በባህላዊ ጉዳዮች ላይ ለመሳተፍ እንደ ክፍተት የሚቆጥሩት ምንድን ነው?
11. የግጭት እና የኮቪድ-19/ቀውሶችን ተፅእኖ ለማሸነፍ ምን እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ብለው ያስባሉ?

# የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ

## የቃለ መጠይቅ መመሪያ ለሴቶች ፣ ህጻናት እና ወጣቶች ቢሮ አመራሮች

የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ ኮቪድ-19 እና ግጭት በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያስከትሉትን ተፅእኖ ለመገምገም ሃላፊነት የተሰጠው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር (EWLA) ብሔራዊ አማካሪ ድርጅት ነው። በመሆኑም ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነተኛ መልስ ለመስጠት የሚያደርጉልን ትብብር ለዚህ ግምገማ ስኬታማነት በጣም አስፈላጊ ነው። ምላሾችዎ ሚስጥርንነታቸው ተጠብቆ ይያዛሉ። ይህም ለኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ተሳትፎ ብቻ የሚውል መሆኑን እያሳወቅን ለትብብርዎ በቅድሚያ እናመሰግናለን!

1. የኢትዮጵያን የፖለቲካ ምህዳር ከሴቶች አንፃር እንዴት ያዩታል? ሴቶች ወደ ፖለቲካ መድረክ እንዲገቡ የሚያበረታታው እንዴት ነው?
2. የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲወዳደር እንዴት ያዩታል?
3. የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ከወንዶች ጋር ሲወዳደር ለሴቶች በቂ እድል ይሰጣል ብለው ያስባሉ? ካልሆነ ለምን?
4. በኢትዮጵያ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደናቅፉ ነገሮች ምንድን ናቸው? በዋናነት በችግር ጊዜ?
5. ከሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እና ከግጭት አፈታት አንፃር ህብረተሰቡ ስላለው አመለካከት ምን ያስባሉ?
6. ግጭቶች በአካባቢዎ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያደርሱትን ተጽእኖ እንዴት ይገልጹታል? በአከባቢዎ በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የግጭት ተፅእኖን እንዴት ይገልፃሉ፡-

- ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንደ አካላዊ ጥቃት፣ ማስፈራራት፣ ጾታዊ ትንኮሳ እና ሌሎች ጾታዊ ጥቃት ከኮቪድ-19 ወዲህ ጨምረዋል?
- ደህንነት/አለመተማመን ፣ በዋነኛነት ለሴቶች ፣ በቅድመ ግጭት፣ በግጭት እና በድህረ ግጭት ጊዜ በአካባቢያችሁ? የመንቀሳቀስ ደህንነት? የህዝብ ንቅናቄ ደህንነት? ሴቶቹ በግጭት ወቅት ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው? ሴቶቹ እንዴት እና ለምን አይነት አደጋ ተጋላጭ ነበሩ? የጥቃት ተጋላጭነት? ሴቶቹ በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ እና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ዋስትና ተሰጥቷቸዋል?
- በግጭት ወቅት በዋናነት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ? ሴቶቹ በግጭት ውስጥ ሲሳተፉ ኖረዋል? እንዴትስ ተሳትፈዋል?

- በግጭት ወቅት የምክክር ደረጃ? በግጭት ወቅት የሴቶች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እንዴት ነበር? በግጭት ወቅት የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቱ አሳታፊ ነበር? በግጭት ወቅት ሴቶችን በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ማግለል የነበረ ይመስልዎታል ፣ በዋነኛነት በአጣዳፊነት?
- ሴቶቹ በግጭት ምክንያት የቤተሰብ ኃላፊነት የተጫነባቸው ይመስልሃል? ሴቶች በችግር/በቀውስ አያያዝ ሂደት ውስጥ እንዴት ተሳትፈዋል? በግጭት ወቅት በቤተሰብ እና በቢሮ ውስጥ የነበራቸው ሚና ምን ነበር?
- በግጭት ወቅት በአመራርዎ ውስጥ የግንኙነት/የተግባቦት ሁኔታ እንዴት ነበር? በቋንቋ ረገድ ግንኙነቱ ግልጽ ነበር? የመገናኛ ብዙሃን ለሴቶች ምቹ ነበሩ? መረጃ ተደራሽ፣ ወቅታዊ፣ ትክክለኛ ነበር?

7. እንደ የካቢኔ ድርሻ ፣ የክልል ምክር ቤት ድርሻ ፣ የአስተዳደር ምክር ቤት ወይም የዘርፍ ውክልና ድርሻ የሴቶችን የአመራር ቦታዎች ላይ የግጭት ተጽእኖ እንዴት ያዩታል? ሴቶች በአመራር ቦታዎች ያላቸውን ድርሻ ከግጭት በፊት ከነበረው ሁኔታ ጋር እንዴት ያወዳድራሉ?

8. ኮቪድ-19 በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ያለውን ተጽእኖ እንዴት ያዩታል? (በተለይ 6ኛውን ሀገር አቀፍ ምርጫ ማካሄድ)? ኮቪድ-19 የሴቶችን በፖለቲካ ውስጥ የመሳተፍ አቅማቸውን እንዴት ቀነሰው? (በተለይ 6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ)? በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሴቶችን እንቅስቃሴ እና ደህንነት ገድቦ ነበር?

9. የኮቪድ-19 ምላሽ ኮሚቴ ስብጥር እንዴት ነበር? ፆታን ያካተተ ነበር?

10. በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ተግባራት የሴቶችን ተሳትፎ እንዴት ያዩታል? በእርስዎ አካባቢ ሴቶች በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ እንዴት ይሳተፋሉ? በሰላም ግንባታ ተግባራትስ እንዴት ይሳተፋሉ?

11. ሴቶች በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ተግባራት ፣ በፖሊሲ ፣ በባህላዊ ተሳትፎ ውስጥ እንዲሳተፉ እንደ ክፍተቶች ምን ምን ጉዳዮች ይመለከታሉ?

12. የግጭት እና የኮቪድ-19/ድንጋጤዎችን ተፅእኖ ለማሸነፍ ምን እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ብለው ያስባሉ?

13. ችግሩን ለመፍታት የቢሮዎ ሚናዎች ምንድን ናቸው?

# የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ

## የቃለ መጠይቅ መመሪያ ለክልል ፣ ለዞን እና ለወረዳ አመራሮች

የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ ኮቪድ-19 እና ግጭት በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያስከትሉትን ተፅእኖ ለመገምገም ሃላፊነት የተሰጠው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር (EWLA) ብሔራዊ አማካሪ ድርጅት ነው። በመሆኑም ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነተኛ መልስ ለመስጠት የሚያደርጉልን ትብብር ለዚህ ግምገማ ስኬታማነት በጣም አስፈላጊ ነው። ምላሾችዎ ሚስጥርነታቸው ተጠብቆ ይያዛሉ። ይህም ለኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ተሳትፎ ብቻ የሚውል መሆኑን እያሳወቅን ለትብብርዎ በቅድሚያ እናመሰግናለን!

1. የኢትዮጵያን የፖለቲካ ምህዳር ከሴቶች አንፃር እንዴት ያዩታል? ሴቶች ወደ ፖለቲካ መድረክ እንዲገቡ የሚያበረታታው/የሚበረታታው እንዴት ነው?
2. የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲወዳደር እንዴት ያዩታል?
3. የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ከወንዶች ጋር ሲወዳደር ለሴቶች በቂ እድል ይሰጣል ብለው ያስባሉ? ካልሆነ ለምን?
4. በአካባቢያችሁ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደናቅፉ ነገሮች ምንድን ናቸው? በዋናነት በችግር ጊዜ?
5. ግጭቶች በአካባቢዎ በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ያላቸውን ተጽእኖ እንዴት ይገልጹታል፡-

- እንደ አካላዊ ጥቃት፣ ማስፈራራት፣ ጾታዊ ትንኮሳ እና ሌሎች ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ከግጭት/COVID-19 ጀምሮ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንዴት ጨመሩ?
- በአከባቢያችሁ በቅድመ ግጭት፣ በግጭት እና በድህረ ግጭት ወቅት በሴቶች ላይ የነበረው ደህንነት/አስተማማኝ ሁኔታ እንዴት ነበር? በዋናነት፣ ለሴቶች እንቅስቃሴ፣ የህዝብ ንቅናቄ? በግጭት ወቅት የሴቶች ተጋላጭነት እንዴት ነበር? ሴቶቹ እንዴት እና ለምን አይነት አደጋ ተጋላጭ ነበሩ? ለጥቃት ተጋላጭነት? ሴቶቹ በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ እና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ዋስትና ተሰጥቷቸዋል?
- በግጭት ወቅት በዋናነት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ? ሴቶቹ በግጭት ውስጥ ሲሳተፉ ኖረዋል? እንዴትስ ተሳትፈዋል?
- በግጭት ወቅት የምክክር ደረጃ? የሴቶች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እንዴት ነበር? የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቱ አሳታፊ ነበር? በግጭት ወቅት ሴቶችን በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ማግለል የነበረ ይመስልዎታል፣ በዋነኛነት በአጣዳፊ/አስቸኳይ ሁኔታ?

- ሴቶቹ በግጭት ምክንያት የቤተሰብ ኃላፊነት የተጫነባቸው ይመስልዎታል? ሴቶች በችግር አያያዝ ውስጥ እንዴት ተሳትፈዋል? በግጭት ወቅት በቤተሰብ እና በቢሮ ውስጥ የነበራቸው ሚና ምን ነበር?
- በግጭት ወቅት በአመራርዎ ውስጥ የግንኙነት/የተግባቦት ሁኔታ እንዴት ነበር? በቋንቋ ረገድ ግንኙነቱ ግልጽ ነበር? የመገናኛ ብዙሃን ለሴቶች ምቹ ነበሩ? መረጃው ተደራሽ፣ ወቅታዊ፣ ትክክለኛ ነበር?

6. እንደ የካቢኔ ድርሻ፣ የክልል ምክር ቤት ድርሻ፣ የአስተዳደር ምክር ቤት ወይም የዘርፍ ውክልና ድርሻ ባሉ የሴቶች የአመራር ቦታዎች ላይ ግጭቶች የሚያደርሱትን ተጽእኖ እንዴት ያዩታል? ሴቶች በአመራር ቦታዎች ያላቸውን ድርሻ ከግጭት በፊት ከነበረው ሁኔታ ጋር እንዴት ያወዳድራሉ?
7. ግጭቱ/ኮቪድ-19 በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ያለውን ተጽእኖ እንዴት ያዩታል? (በ6ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ ወቅት)? ኮቪድ-19 የሴቶችን በፖለቲካ ውስጥ የመሳተፍ አቅማቸውን እንዴት ነበር የቀነሰው? (በተለይ በ6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ)? በፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሴቶችን እንቅስቃሴ እና ደህንነት ገድቦ ነበር?
8. የኮቪድ-19 ምላሽ ሰጪ ኮሚቴ ስብጥር እንዴት ነበር? ፆታን ያካተተ ነበር?
9. በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ተግባራት የሴቶችን ተሳትፎ እንዴት ያዩታል? በእርስዎ አካባቢ ሴቶች በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ እንዴት ይሳተፋሉ? በሰላም ግንባታ ተግባራት እንዴት ይሳተፋሉ?
10. ሴቶች በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ተግባራት፣ በፖሊሲ፣ በባህላዊ ተሳትፎ ውስጥ እንዳይሳተፉ እንደ ክፍተት የሚቆጥሩት ምንድን ነው?
11. የግጭት እና የኮቪድ-19/ድንጋጤዎችን ተፅእኖ ለማሸነፍ ምን እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ብለው ያስባሉ?
12. ችግሮቹን ለመፍታት የቢሮዎ ሚናዎች ምንድን ናቸው?

# የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ

## የቃለ መጠይቅ መመሪያ-ለፖለቲካ ፓርቲዎች እና ምክር ቤት አባላት

የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ ኮቪድ-19 እና ግጭት በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያስከትሉትን ተፅእኖ ለመገምገም ሃላፊነት የተሰጠው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር (EWLA) ብሔራዊ አማካሪ ድርጅት ነው። በመሆኑም ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነተኛ መልስ ለመስጠት የሚያደርጉልን ትብብር ለዚህ ግምገማ ስኬታማነት በጣም አስፈላጊ ነው። ምላሾችዎ ሚስጥርንነታቸው ተጠብቆ ይያዛሉ። ይህም ለኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ተሳትፎ ብቻ የሚውል መሆኑን እያሳወቅን ለትብብርዎ በቅድሚያ እናመሰግናለን!

1. በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ እንዴት ያዩታል?
2. የፓርቲያችሁን የፆታ ስብጥር እንዴት ያዩታል?
3. በፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች እና ዘመቻዎች ውስጥ በንቃት እየተሳተፍኩ ነው ብለው ያስባሉ?
4. በኮቪድ-19 እና በአካባቢው በተከሰተው ግጭት/የፀጥታ ችግር ምክንያት የሴት ፖለቲከኞች ከስልጣን ማፈግፈግ ነበር?
5. ግጭት በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ እንዴት ያዩታል?

- ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንደ አካላዊ ጥቃት ፣ ማስፈራራት ፣ ጾታዊ ትንኮሳ እና ሌሎች ጾታዊ ጥቃት ከኮቪድ-19 ወዲህ ጨምረዋል?
- ደህንነት/አለመተማመን ፣ በዋነኛነት ለሴቶች ፣ በቅድመ ግጭት ፣ በግጭት ወቅትና በድህረ ግጭት በአካባቢያችሁ ለሴቶች የመንቀሳቀስ ደህንነት? የሴቶች የህዝብ ንቅናቄ ደህንነት? ሴቶቹ በግጭት ወቅት ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው? እንዴት እና ለምን አይነት አደጋ ተጋላጭ ነበሩ? የጥቃት ተጋላጭነት? በነፃነት ለመንቀሳቀስ እና ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ዋስትና አግኝተዋል?
- በግጭት ወቅት በዋናነት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ? ሴቶቹ በግጭት ውስጥ ሲሳተፉ ኖረዋል? እንዴትስ ተሳትፈዋል?
- በግጭት ወቅት የምክክር ደረጃ? በግጭት ወቅት ሴቶች በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ለማድረግ ፓርቲያችሁ የተጠቀመበት ዘዴ ምን ነበር? በግጭት ወቅት የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቱ አሳታፊ ነበር? በግጭት ወቅት ሴቶችን በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ማግለል የነበረ ይመስልዎታል፣በዋነኛነት በአጣዳፊነት?
- በግጭት ምክንያት የቤተሰብ ኃላፊነት በሴቶች ላይ ተጭኗል? በችግር አያያዝ ውስጥ ይሳተፋሉ?

- በግጭት ወቅት በአመራርዎ ውስጥ የግንኙነት/የተግባቦት ሁኔታ እንዴት ነበር? በቋንቋ ረገድ ግንኙነቱ ግልጽ ነበር? የመገናኛ ብዙሃን ለሴቶች ምቹ ነበሩ?
- ልዩነት አለ? ከቁጥር እና ከተሳትፎ አንፃር? ከግጭት በፊት፣ በግጭት ወቅት እና በኋላ?

6. በአካባቢያችሁ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደናቅፉ ምን ችግሮች አሉ ብለው ያስባሉ?
7. በተለይም በቀውስ/በችግር ጊዜ እና ከችግር በኋላ ህብረተሰቡ በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ያለውን አመለካከት እንዴት ያዩታል?
8. እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ምን ይመክራሉ?

# የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ

## የቃለ መጠይቅ መመሪያ-ለምርጫ ቦርድ

የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ ኮቪድ-19 እና ግጭት በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያስከትሉትን ተፅእኖ ለመገምገም ሃላፊነት የተሰጠው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር (EWLA) ብሔራዊ አማካሪ ድርጅት ነው። በመሆኑም ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነተኛ መልስ ለመስጠት የሚያደርጉልን ትብብር ለዚህ ግምገማ ስኬታማነት በጣም አስፈላጊ ነው። ምላሾችዎ ሚስጥርንነታቸው ተጠብቆ ይያዛሉ። ይህም ለኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ተሳትፎ ብቻ የሚውል መሆኑን እያሳወቅን ለትብብርዎ በቅድሚያ እናመሰግናለን!

1. ከሴቶች ጋር በተያያዘ ጉዳዮችን ለማስተናገድ የተለየ አሰራር አለዎት?
2. በኢትዮጵያ ውስጥ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ እንዴት ያዩታል?
3. ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች የፆታ ስብጥር ምን ያስባሉ?
4. የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደናቅፉ ነገሮች ምንድን ናቸው ብለው ያስባሉ?
5. ከግጭት በፊት፣ በግጭት ወቅት እና በኋላ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ እንዴት ያዩታል? ልዩነት አለ? ከቁጥር እና ከተሳትፎ አንፃር?
6. ፆታን መሰረት ባደረገ ጥቃት፣ ተጋላጭነት፣ ደህንነት፣ የውሳኔ አሰጣጥ ላይ ምክክር፣ የግንኙነት መስመር፣ የቤተሰብ ኃላፊነት ግጭቶች በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያደርሱትን ተጽእኖ እንዴት ያዩታል?
7. በግጭት አፈታት የሴቶችን ተሳትፎ እንዴት ያዩታል? ሁኔታው ወደ ፊት እንዲመጡ ያስችላቸዋል?
8. የሰሜኑ ግጭት በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እና ግጭት አፈታት ላይ ተጽእኖ እያሳደረ ነው ብለው ያስባሉ? እንዴት?
9. ስለዚህ ግጭትና ስለ 6ኛው አገራዊ ምርጫ ምን ያስባሉ?
10. ምርጫ ቦርድ ፈተናዎቹን ለመቋቋም ምን አድርጓል?
11. ከሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ እና ግጭት አፈታት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ምን አስተያየት ይሰጣሉ?

# የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ

## የቃለ መጠይቅ መመሪያ-መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች

የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ ኮቪድ-19 እና ግጭት በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያስከትሉትን ተፅእኖ ለመገምገም ሃላፊነት የተሰጠው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር (EWLA) ብሔራዊ አማካሪ ድርጅት ነው። በመሆኑም ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነተኛ መልስ ለመስጠት የሚያደርጉልን ትብብር ለዚህ ግምገማ ስኬታማነት በጣም አስፈላጊ ነው። ምላሾችዎ ሚስጥርንነታቸው ተጠብቆ ይያዛሉ። ይህም ለኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ተሳትፎ ብቻ የሚውል መሆኑን እያሳወቅን ለትብብርዎ በቅድሚያ እናመሰግናለን!

1. በግጭት እና በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት ያዩታል?
2. የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ እንዴት ያዩታል? በዋናነት በግጭት/ኮቪድ-19 ወቅት የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ከወንዶች ጋር እንዴት ያወዳድራሉ?
3. ፆታን መሰረት ባደረገ ጥቃት ተጋላጭነት፣ ደህንነት ፣ የውሳኔ አሰጣጥ ላይ ምክክር ፣ የግንኙነት/የተግባቦት ሁኔታ፣ የቤተሰብ ሃላፊነት/ሸክምን በተመለከተ ግጭቶች በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያሳድሩትን ተፅእኖ እንዴት ያዩታል?
4. በግጭት ፣ በኮቪድ-19 ፣ በሰላም ግንባታ እና በግጭት አፈታት ወቅት የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማጎልበት የተነደፉ ፕሮጀክቶች አሉዎት? ምን ስኬቶችን አረጋግጠዋል?
5. በፖለቲካ ተሳትፎና በግጭት አፈታት እንቅስቃሴዎች ውስጥ በወንዶች እና በሴቶች መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት አለ?
6. በሰላም ግንባታ እና በግጭት አፈታት የሴቶችን ሚና እንዴት ያዩታል?
7. ሴቶች በሰላም ግንባታ እና በግጭት አፈታት ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ የሚያደናቅፉ ነገሮች ምንድን ናቸው ብለው ያስባሉ?
8. ኮቪድ-19 በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ምን ተጽዕኖ አሳድሯል ብለው ያስባሉ?
9. ችግሮቹን ለማቃለል ምን መደረግ አለበት?

# የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ

## የቃለ መጠይቅ መመሪያ-ለምሁራን እና ተመራማሪዎች

የምስራቅ አፍሪካ አማካሪ ኮቪድ-19 እና ግጭት በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያስከትሉትን ተፅእኖ ለመገምገም ሃላፊነት የተሰጠው የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር (EWLA) ብሔራዊ አማካሪ ድርጅት ነው። በመሆኑም ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነተኛ መልስ ለመስጠት የሚያደርጉልን ትብብር ለዚህ ግምገማ ስኬታማነት በጣም አስፈላጊ ነው። ምላሾችዎ ሚስጥርንነታቸው ተጠብቆ ይያዛሉ። ይህም ለኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ተሳትፎ ብቻ የሚውል መሆኑን እያሳወቅን ለትብብርዎ በቅድሚያ እናመሰግናለን!

1. የኢትዮጵያን የፖለቲካ ምህዳር ከሴቶች አንፃር እንዴት ያዩታል? ሴቶች ወደ ፖለቲካ መድረክ እንዲገቡ የሚያበረታታው እንዴት ነው?
2. የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲወዳደር እንዴት ያዩታል?
3. የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ከወንዶች ጋር ሲወዳደር ለሴቶች በቂ እድል ይሰጣል ብለው ያስባሉ? ካልሆነ ለምን?
4. በኢትዮጵያ የእርስዎን/የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያደናቅፉ ነገሮች ምንድን ናቸው? በዋናነት በቀውስ ጊዜ?
5. ከሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎና የግጭት አፈታት አንፃር ህብረተሰቡ ስላለው አመለካከት ምን ያስባሉ?
6. ግጭቶች በአካባቢዎ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያደርሱትን ተጽእኖ እንዴት ይገልጹታል? በአከባቢዎ በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የግጭት ተፅእኖን እንዴት ይገልፃሉ፡-

- ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እንደ አካላዊ ጥቃት፣ ማስፈራራት፣ ጾታዊ ትንኮሳ እና ሌሎች ጾታዊ ጥቃት ከኮቪድ-19 ወዲህ ጨምረዋል?
- ደህንነት/አለመተማመን፣በዋነኛነት ለሴቶች በቅድመ ግጭት፣ በግጭት ጊዜ እና በድህረ ግጭት በአካባቢያችሁ የመንቀሳቀስ ደህንነት? የህዝብ ንቅናቄ ደህንነት? የጥቃት ተጋላጭነት?
- በግጭት ወቅት በዋናነት በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ?
- በግጭት ወቅት የምክክር ደረጃ?
- በግጭት ምክንያት የቤተሰብ ኃላፊነት?

7. እንደ የካቢኔ ድርሻ፣ የክልል ምክር ቤት ድርሻ፣ የአስተዳደር ምክር ቤት ወይም የዘርፍ ውክልና ድርሻ በሴቶችን የአመራር ቦታዎች ላይ የግጭት ተጽእኖን እንዴት ያዩታል? ሴቶች በአመራር ቦታዎች ያላቸውን ድርሻ ከግጭት በፊት ከነበረው ሁኔታ ጋር እንዴት ያወዳድራሉ?
8. ኮቪድ-19 በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ያለውን ተጽእኖ እንዴት ያዩታል? በፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሴቶችን ደህንነት፣ እንቅስቃሴ እና ሰላም ገድቧል?
9. በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ተግባራት የሴቶችን ተሳትፎ እንዴት ያዩታል? በእርስዎ አካባቢ ሴቶች በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ እንዴት ይሳተፋሉ? በሰላም ግንባታ ተግባራትስ እንዴት ይሳተፋሉ?
10. ሴቶች በግጭት አፈታት እና በሰላም ግንባታ ተግባራት፣ በፖሊሲ፣ በባህላዊ ጉዳዮች ላይ ለመሳተፍ እንደ ክፍተት የሚቆጥሩት ምንድን ነው?
11. የግጭት እና የኮቪድ-19/ስጋቶች በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ለማሽነፍ ምን እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ብለው ያስባሉ?



Photos[1]
Focus at Borena, Oromia Regional state

[1]Afar, Women informants were Muslim and not volunteer to take photo.



Photos[2]
FGDs at Gimbi , Oromia Regional state

# በአድራሻዎቻችን ያግኙን

**የቢሮ አድራሻችን፡-** አዲስ አበባ ፡ ቂርቆስ ክፍለ
ከተማ ፡ ሜክሲኮ/ቡልጋሪያ አካባቢ ከሚገኘዉ
ሚካኤል ቤተክርስቲያን አጠገብ
**ስ.ቁ፡-** +251-11-508783
**ኢሜል፡-** info@ewla-et.org
**ፖ.ሳ.ቁ፡-** 13760

USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE
NDI NATIONAL DEMOCRATIC INSTITUTE
የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር
Ethiopian Women Lawyers' Association